


**ሥዕል 7፡- ምስለ ፍቁር ወልዳ (እመቤታችን ከተወዳጁ ልጇ ጋር)**

"ስክሲስ ምክሕነ፡፡ ወቀዳሚተ መድኃኒትነ፡፡ ወመሠረተ ንጽሕነ፡፡ ኮነ በማርያም ድንግል፡፡ እንተ ወለደት ለነ ዘእግዚአብሔር ቃለ፡፡"

"የመመኪያችን ዘውድ፣ የደኅንነታችን መጀመሪያ፣ የንጽሕናችንም መሠረት አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድን በወለደችልን በድንግል ማርያም ሆነልን፡፡"

(ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 44-46)



# ምዕራፍ አራት

## 4. የወላዲተ አምላክ ዘለዓለማዊ ድንግልና ከምሥጢረ ድኅነት ጋር ያለው ጥልቅ ግንኙነት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማር ያም ዶግማ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድን ግልና አንዱና ዋነኛው ክፍለ ትምህርት ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊ የነገረ ማር ያም አስተምህሮን ልዩ ከሚያደርጉት ዐበይት ምሥጢራት መካከል ወላዲተ አምላክ ድንግል በክልኤ [Dual Virgin] የመባሏ ምሥ ጢር ነው፡፡ ቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም ዘለዓለማዊት ድንግል መሆኗን የሚመሰክረው የቤተ ክርስቲያናችን መሠረተ እምነት የመድ ኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የሚያረጋግጥ በመ ሆኑ ከነገረ ድኅነት ጋር የተያያዘ ሰፊና ጥልቅ ምሥጢር አለው፡፡[201]

ይህንን መሠረታዊ የነገረ መለኮት አስተምህሮ በማጉላትና በማጽናት በ553 ዓ.ም. የተደረገውና ካልዕ ጉባኤ ቁስጥንጥንያ [The Fifth Ecumenical Council of Constantinople II] በመባል የሚታወቀው አምስተኛው ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እመቤታችንን ወት ረ ድንግል ማርያም፤ ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም [Ever- Virgin Mary] ወይም በግሪክ *Aeiparthenos* የሚል ልዩ ስያሜ በመስጠት ዘለዓለማዊ

(201) ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ [Emperor Zara Yacob]፣ *"መጽሐፈ ብርሃን" ["The Book of Light"] CSCO*፣ ገጽ 70-73፡፡ ቅዱስ መቃርስ፣ "በእንተ ምሥጢረ ሥላሴ"፣ *ሃይማኖተ አበው*፣ ገጽ 437፡፡ Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia*, 71-93. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 184-185፡፡ Abba Melketsedek, *The Teaching of the Ethiopian Orthodox Church*, 69-70. John Hainsworth, "The Ever-Virginity of the Mother of God," *Canadian Orthodox Messenger Quarterly*, v. XV, No. 1 (Winter, 2003/ 2004), 5.

ድንግልናዋን በይፋ አረጋግጧል:: ከዚህ ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ዘላለማዊት ድንግል የመሆኗ ምሥጢር በሰፊው የታወቀና የተረዳ በእጅጉም የተከበረ ኦርቶዶክሳዊ እምነትና ሐዋርያዊ ትምህርት መሆኑን ልብ ይሏል::[202] በነገረ ማርያም የትምህርት ዘርፍ ጥናትና ምርምር ያደረጉ አያሌ የሥነ መለኮት ሊቃውንት የመድኅነ ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስን ድንግልናዊ ጽንስና ልደት «የምሥጢረ ሥጋዌ አንኳር ምሥጢር» በማለት ይገልጹታል::[203]

## 4.1 የዐሥራው መጻሕፍት ምስክርነት

ኦርቶዶክሳውያን መተርጉማን በዘመነ ብሉይ በተለያየ ኅብረ አምሳል የተገለጸውንና በብዙ ዓይነት ኅብረ ትንቢት የተነገረውን የሥጋዌ ምሥጢር በዘመነ ሐዲስ ከተፈጸመው አምላካዊ የድኅነተ ዓለም ሥራ ጋር በማገናዘብ የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና አምልተውና አስፍተው አስተምረዋል:: ከእነዚህ አያሌ ምሳሌዎችና ትንቢቶች መካከል ከነገረ ድኅነት ጋር የተያያዘ ዘርፈ ብዙ ትርጓሜና ጥልቅ ምሥጢር ያላቸውን ማለትም:- ዳግሚት ኅትምት ምድር፣ በትረ አሮን፣ ፀምር ዘጌዴዎን፣ የተዘጋች የሕዝቅኤል ምሥራቃዊት ጥኅት (ደጃፍ) እንዲሁም ደብር ነዋኅ ዘዳንኤል የተሰኙትን እንመለከታለን::

### 4.1.1 ዳግሚት ኅትምት ምድር

የሥነ ፍጥረትን የት መጣና ህልውና በስፋት የሚያትተው የቅዱስ መጽሐፍ ክፍል እንደሚያስረዳን ፈጣሬ ፍጥረታት የሆነው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር «ስታብቊል ምድር፤ ምድርም ታብቅል» ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት የመጀመሪያይቱ ኅትምት (ድንግል)

[202] Davis, *The Seven Ecumenical Councils (325-387): Their History and Theology,* 244. Bloosper, *The Virgin Birth,* 46. Gaventa, *Mary: Glimpses of the Mother of Jesus,* 12.

[203] Hilda Graef, *Devotion to the Blessed Virgin* (London: Hawthorn Books Inc., 1963), 31. Gaventa, *Mary: Glimpses of the Mother of Jesus,* 16.



መሬት ዘር ሳይወድቅባት፣ ገበሬ ሳይግርባትና ሳይጥርባት፣ ዝናብ ሳያስፈልጋት ለፍጥረታት ሁሉ ምግብ የሚሆኑ ዕፅዋቱን፣ አዝርዕቱንና አትክልቱን አስገኝታለች:: (ዘፍ. 1÷11-12) እንደዚሁም አማናዊቷ ዳግሚት ኅትምት ምድር የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ሰማደ አንስት (የሴቶች ልማድ) ሳያገኛት፣ ዘርዐ ብእሲ (የወንድ ዘር) ሳያርፍባትና ምክንያት ሳይሆናት ፍሬ ሕይወት የሚሆን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ድንግልና ወልዳ አስገኝታልናለች:: ከእርሷ እንበለ ዘርዕ (ያለ ዘር)፣ እንበለ ሩካቤ (ያለ ግንኙነት) የተገኘው ዳኅየዊ (አዳኙ) ጌታም ዕፀ ሕይወት ወዕፀ መድኃኒት በሆነው በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ኅብስተ ሕይወት ቅዱስ ሥጋውን በመቁረስ፣ ማየ ሕይወት ደሙን በማፍሰስ ለዘላለማዊ ሕይወትና ለሰማያዊው ክብር የምንበቃበትን ምግበ ነፍስ በጸጋ ሰጥቶናል::[204]

ይህንን ግሩምና ድንቅ ምሥጢር አስመልክቶ ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ሲናገር «ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ዘእንበለ (ገበሬ) ፈጽማ የማታውቅ እርሻ ናት፤ ከእርሷም ምሉዓ በረከት፣ ምሉዓ ጸጋ የሆነ ፍሬ በረከት ጌታ ወጣ፣ ተገኘ:: በዚህም ምክንያት ያለ አንዳች ዘር ለፍጥረት ሁሉ ምግብ የሚሆን አማናዊ ፍሬ ሕይወት ጌታን አስገኘች»[205] በማለት መስክሯል:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ምሥጢር ገልጾ በመዋዕለ ስብከቱ ሲያስተምር «ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፣ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ:: ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው:: ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ::» (ዮሐ. 6÷54-56) በማለት በአጽንኦት ተናግሯል:: በዚህም አምላካዊ ቃል አማናዊቷ ኅትምት ምድር ቅድስት ድንግል

[204] St. Jacob of Serug, *On the Mother of God,* 70. Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers,* 43.

[205] Brock, *Bride of Light,* 35, 85, 94. ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣* ገጽ 386:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን፣* ገጽ 231::

እመቤታችን ከመጀመሪያይቱ ምድር እጅግ የበለጠችና የከበረች መሆኗን እንመለከታለን:: ምክንያቱም የመጀመሪያዋ ምድር ያበቀለች ውና ያፈራችው ምግበ ሥጋ የሚሆኑ ፍጥረታትን ሲሆን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የወለደችውና ያስገኘችው ግን ምግበ ነፍስ የሆነውን አምላክ በመሆኑ ነው::

ከላይ የገለጥነውን ምሥጢረ ድኅነት አስመልክቶ በኦርቶ ዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ዘወትር የሚዘመረው የእመቤ ታችን ምስጋና «አንቲ ውእቱ ገራህት ዘኢተዘርአ ውስቴታ ዘርዕ:: ወጽአ እምኔኪ ፍሬ ሕይወት፤ ዘር ያልወደቀባት፣ ገበሬ ያልጣረባትና ያልጋረባት፤ ስታብቁል (ታብቅል) ባለው አምላካዊ ቃል ከልምላሜ፤ ከጽጌ፤ ከፍሬ ደርሳ የተገኘች ገራህተ ሠሉስ (የማክሰኞ ዕለት እርሻ) አንቺ ነሽ»(206) በማለት ተናግሮላታል:: ይህ ቃለ ውዳሴ ወላዲተ አምላክን ከመጀመሪ ያይቱ ኅትምት ምድር ሲለያት ፍሬ ሕይወት የሚሆን ጌታ ካንቺ ተገኘ ፣ ተወለደ ብሎ በምሥጢር ይገልጻታል:: በእመቤታችንና በገራህተ ሠሉስ መካከል ያለው ሌላው አስደሳች ምሥጢራዊ ንጽጽር ደግሞ የመጀመሪ ያይቱ ኅትምት ምድር ከሃሊ ኩሉ የሆነው ፈጣሬ ፍጥረታት እግዚአብሔ ር «ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ፤ እንዲሁም ሆነ::» (ዘፍ. 1÷11) ብሎ በተናገረ ጊዜ ምግበ ሥጋ የሚሆኑ ዕፅዋትን፣ አዝርእትንና አትክልትን አብቅላለች፤ አፍርታለች::

በአንጻሩ ደግሞ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምም የመልአከ ሰላም የቅዱስ ገብርኤልን ቃለ ብሥራት ሰምታ «ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፣ ይደረግልኝ» (ሉቃ. 1÷38) ባለች ጊዜ ዘር፣ ሩካቤ ምክንያት ሳይሆናት መብልዐ ጽድቅ ወስቴ ሕይወት ዘበአማን የሆነውን ፍሬ ሕይወት ጌታን አስገኝታለች:: በዚህም ንጽጽራዊ ትርጓሜ መሠረት በዕለተ ፍጥረት «ስታብቁል፣ ስይኩን» የሚለው የፈጣሪ ቃል ፍጥረታትን እንዳስገኘና ወደዚህ ዓለም እንዳመጣ ሁሉ፤ በዕለተ

(206) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 52::*



ብሥራት «ይኩነኒ» የሚለው የፍጡር (የእመቤታችን) ቃለ ተአምኖ ፈጣሪን ወደዚህ ዓለም አምጥቶአል:: ስለሆነም በጥንተ ተፈጥሮ «ስይኩን» የሚለው መለኮታዊ ቃል ለፍጡራን መገኘትና ወደዚህ ዓለም መምጣት ምክንያትና መሠረት እንደሆነ ሁሉ፤ «ይኩነኒ» የሚለው የወላዲተ አምላክ የእምነት ቃልና በጎ ፈቃድ ደግሞ ለሐዲስ ተፈጥሮ (ለድኅነተ ዓለም) ምክንያትና መሠረት ሆኗል::(207)

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም ትምህርት ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም «ኅትምት ምድር» የተሰኘችበት ሌላው ምሥጢር ደግሞ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጸውንና በቀዳማዊው አዳምና [First Adam] በዳግማዊው አዳም [Second Adam] በኢየሱስ ክርስቶስ መካከል ያለውን ንጽጽር መሠረት በማድረግ ነው:: ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ምሥጢር ሲያስረዳ «... ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና:: ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና:: ... እንዲሁ ደግሞ:- ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ:: ... የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታ ዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው:: ... የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን» (1ኛ ቆሮ. 15÷21-22፣ 45፣ 47፣ 49) በማለት አፍታቶና አብራርቶ ተናግሮአል::

መጻሕፍት አምላካውያት ቀዳማዊው አዳም እንበለ ዘርዕ ከኅት ምት ምድር መገኘቱን በግልጽ ይመሰክራሉ:: ለዚህም «እግዚአብ ሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው» (ዘፍ. 2÷7)፤ «አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህ» (ዘፍ. 3÷19)፤ «አቤቱ፣ እኛ አፈር እንደ ሆንን አስብ» (መዝ. 102÷14) የሚሉት ቃላተ መጻሕፍት በቂ ማስረጃዎች

(207) St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 19, 45. *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 52-53::*

ናቸው:: በመሆኑም የመጀመሪያይቱ ምድር ከቀዳማዊው አዳም በፊት
ም ሆነ በኋላ ሌላ ሰው አላስገኘችም:: እንደዚሁም ሁሉ አማናዊት ኅት
ምት ምድር የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከዳግማ
ዊው አዳም ከኢየሱስ ክርስቶስ በፊትም ሆነ በኋላ ሌላ ልጅ አልወለደ
ችም፣ የላትምም::

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ስለዚህ ምሥጢር ሲናገር «ሠሪቀ በሥጋ
እምድንግል ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ወእድኃነነ፤ ማኅየዊ የሚሆን ጌታ ዘር
ምክንያት ሳይሆነው ከድንግል በሥጋ ተወልዶ አዳነን»[208] ብሏል::
ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ማኅየዊ ጌታን አስገኘች (ወለደች)
መባሉም በሥጋ ርስት, አንጻር መሆኑን ይመለከቷል:: መጽሐፍ «እኮ
ወለደ ማርያም በመለኮቱ እላ በከመ ሥርዓት ትስብእቱ»[209] እንዳለው
መድኃኒታችን ወልደ ማርያም መባሉም በሥጋዊ ርስት፣ በሥጋዊ
ሥርዓት ነው:: ምክንያቱም ቅድስት ድንግል እመቤታችን አካላዊ ቃል
እግዚአብሔር ወልድን የምትወልደው ከባሕርይዋ በሥጋ ነውና::

አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን
ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ ዘር፣ ያለ ሩካቤ የተወለደው ልደት
ቀዳማዊ ልደቱን ይገልጻል:: ይኸውም ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር አም
ስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ዳግሚት ኅትምት ምድር ከሆነ
ችው ከድንግል ማርያም ያለ አባት መወለዱ፤ ቅድመ ዓለም ከባሕርይ
አባቱ ከአብ ያለ እናት መወለዱን ያጠይቃል:: ይህንን ረቂቅና ጥልቅ
ምሥጢር አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ ሱኑትዩ በሃይማኖተ አበው
ሲመሰክር «ልደት ቀዳማዊ ተዐውቀ በደኃሬዊ ልደት፤ ቀዳማዊ (የመጀመሪ
ያው) ልደት በደኃሬዊ (በሁለተኛው) ልደት ታወቀ፣ ተረዳ»[210] በማለት
አስተምሮአል:: ከዚህም ጋር ኢትዮጵያዊው የሥነ መለኮት ሊቅ

[208] ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 21-23:: Gambero, *Mary and the Fathers of the Church: The Blessed Virgin Mary in Patristic Thought*, 113.
[209] ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 21::
[210] ቅዱስ ሱንትዩ፣ «በእንተ ምሥጢረ ሥላሴ»፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 509-510::



[Ethiopian Theologian] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ «ዘቀዳሚ ልደት አመሥጠ
ረ ወዘደኃሬ ልደት አመንከረ»[211] ብሎአል::

በምዕራፉ መግቢያ ላይ እንደገለጥነው እመቤታችን ቅድስት
ድንግል ማርያምን እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ ናት ብሎ ማመንና
ዘለዓለማዊ ድንግልናዋንም አንዳች ሳይጠራጠሩ መቀበል የልጇ የወዳጇ
የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት፣ ፈጣሪነትና አዳኝነት ማመ
ንና መቀበል ነው:: ዳግመኛም ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «ሶበሰ ተ
ወልደ እግዚእነ በሩካቤ ብእሲ ወብእሲት ዘከማነ ብዙኃን እምተሐዘብዎ ወእምረሰይዎ
ሐሰተ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እኛ በዘር፣ በሩካቤ ተወልዶ
ቢሆን ኖሮ ብዙዎች ዕሩቀ ብእሲ (ፍጡር) ባሉት፤ የአምላክነቱንም
ምሥጢር በሐሰት አሳብለው በተጠራጠሩትና በካዱትም ነበር»[212] ሲል
የተናገረው ይህንኑ እውነታ ለማጉላትና ለማጽናት ነው:: በአጭሩ
ቀዳማዊ አዳም ከኅትምት ምድር መገኘቱ ዳግማዊ አዳም የተባለ ጌታ
በኅቱም ማኅፀን ለመወለዱ ምሳሌ መሆኑን ልብ ይሏል::

በዚህ መሠረት የወላዲተ አምላክ የድንግል ማርያምን ዘለዓለ
ማዊ ድንግልና አምኖ አለመቀበል የመድኅነ ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስን
የባሕርይ አምላክነት መጠራጠርና አለመቀበል ከመሆኑም ሌላ ዳግማዊ
አዳም የተሰኘው ጌታን ከቀዳማዊው አዳም እንደማሳነስም ይቆጠራል::
ይህ ደግሞ የክርስትና እምነት መሠረትና ዐቢይ እውነታ የሆነውን የነገ
ረ ድኅነት ትምህርት ይንደዋል፣ ያፋልሰዋልም:: ይኸውም ዳግማዊው
አዳም ክርስቶስ ቀዳማዊውን አዳም ሊያድነውም ሆነ ሊያከብረው
እንዴት ይችላል? ምክንያቱም የሚያንሰው (ሁለተኛው አዳም) ከእርሱ
የሚበልጠውን (የመጀመሪያው አዳምን) ሊያከብረውና ሊያድነው
አይችልምና ነው:: ስለሆነም ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን

[211] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ «*መጽሐፈ ምሥጢር*» *["The Book of Mystery"]*፣ ገጽ 95::
[212] ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 22:: ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 68:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ «በእንተ ምሥጢረ ተዋሕዶ»፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 240::

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዳግማዊ አዳም ክርስቶስን ከመፅነሷ በፊት (ቅድመ ፀኒስ)፣ በፀነሰችውም ጊዜ (ጊዜ ፀኒስ)፣ ከፀነሰችውም በኋላ (ድኅረ ፀኒስ)፤ እንዲሁም ከመውለዷ በፊት (ቅድመ ወሊድ)፣ በወለደችው ጊዜ (ጊዜ ወሊድ)፣ ከወለደችውም በኋላ (ድኅረ ወሊድ) ተፈትሖ ማኅፀን ሳያገኛት ማለትም ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ በድንግልና ጸንታ የኖረች ወትረ ድንግል ማርያም (ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም) ብላ ታምናለች፣ ታሳምናለች::[213]

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚነግሩን የመጀመሪያው አዳም የተገኘው እርግማን ከሌለባት ንጽሕት ምድር ነው:: ምክንያቱም እርግማን የኃጢአት ፍሬና የበደል ውጤት በመሆኑ መርገም የመጣው በጥንተ ተፈጥሮ በንጹሐ ጠባይዕና በቅድስና ባሕርይ የተፈጠረው የሰው ልጅ በኃጢአቱና በበደሉ ምክንያት ከወደቀ በኋላ ነውና:: ከላይ የተመለከትነው የቀዳማዊ አዳምና የዳግማዊ አዳም ምሥጢራዊ ንጽጽር ሁለተኛው አዳም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስ ከሌለባት፤ ንጹሐ ጠባይዕ፣ ቅድስና ባሕርይ ካላደፈባት ንጽሕትና ኅትምት ምድር ከሆነችው ከቅድስተ ቅዱሳን፣ ከንጽሕተ ንጹሐን ከድንግል ማርያም መወለዱን በግልጥ ያሳያል፣ ያስረዳል::

ቅዱስ አባ ሕርያቆስም «ምእናም አንቲ ዘእምኒኪ ለብሰ አማኑኤል ልብሰተ ሥጋ ዘኢይትፈጸም፤ ባሕርዩ የማይመረመር አማኑኤል የሥጋን ልብስነት ከአንቺ የነሣት (የለበሳት) የድኅነት መሣሪያው አንቺ ነሽ:: አንድም የማይመረመር አማኑኤል የሥጋ አለባበስን የለበሰብሽ የሸማኔ ጉድጓድ አንቺ ነሽ»[214] በማለት አመስግኗታል:: ሊቁ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን በሸማኔ ጉድጓድ የመሰለበት ምሥጢሩ በሸማኔ ጉድጉድ ድርና ማግ እንዲገናኙባትና አንድ እንዲሆኑባት፤ እንደዚሁም

[213] Fulton J. Sheen, *The World's First Love* (New York: McGraw-Hill Book Company, Inc., 1952), 55-56. Brock, *Bride of Light,* 63. Bettenson, *The Early Christian Fathers,* 82-83. Mascall, "The Mother of God", 186-187. ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፣ ገጽ 20-21::

[214] *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 64-65::



ሁሉ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ማኅፀንም የትስብእትና የመለኮት ተዋሕዶ (አንድነት) ተደርጎባታልና ነው::

ዳግመኛም ይኸው ሊቅ «ለፍጹ ገብረ ዘእምጥንተ ሥጋሁ ለአዳም፤ የባሕርዩ ርቀትና ጥልቀት የማይመረመር አማኑኤል መርገም ያልወደቀበትን፣ ንጽሐ ጠባይዕ፣ ቅድስና ባሕርይ ያላደፈበትን ከአዳም ጥንተ ባሕርይ የተገኘ ያንቺን ሥጋና ነፍስ ተዋሐደ» ሲል መስክሮአል:: የኋላ ሊቃውንት መተርጉማን አባ ሕርያቆስ «ዘእምጥንተ ሥጋሁ ለአዳም» ያለውን ሲተረጉሙ ሕገ እግዚአብሔርን ባለመጠበቁና ፈቃደ እግዚአብሔርን በመተላለፉ ምክንያት ብልየት (ዕድፈትና ርኩሰት) አግኝቶት የነበረ የሰው ባሕርይ ተአዛዚተ እግዚአብሔር በሆነችው በእመቤታችን በድንግል ማርያም ባሕርይ ነጽቶ ተገኘ ማለት ነው ብለዋል::

ይህም ትርጓሜ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ «ማርያምሰ ተሐቱ ውስተ ከርሡ ለአዳም ከመ ባሕርይ ፀዓዳ፤ ድንግል ማርያም ግን በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ንጹሕ ዕንቍ ታበራ ነበር»[215] ሲል ከተናገረው ኃይለ ቃል ጋር በምሥጢር የተገናዘበና የተሰናሰለም ነው:: ይኸውም ምሥጢሩ ምንም እንኳን እመቤታችን ከአዳም ባሕርይ የተገኘች ዘርዐ አዳም ብትሆንም ቅሉ የአዳም ገንዘብ የሆነው የኃጢአት ዝገት ከጽርየቷ (ከንጽሐ ጠባይዋና ከቅድስና ባሕርይዋ) አላሳደፋትም:: ምክንያቱም የዕንቍን ባሕርይ የተገኘበት ቦታ ጽርየቱን አይለውጠውምና ነው:: ሌላው ምሥጢር ደግሞ «ጥንቱን በአዳም አደረገ» ማለቱ ሠዓሌ ሕፃናት የሆነው አምላክ ሰው በሆነ ጊዜ ሕፃናት በሚፀነሱበት መጠን ማለትም ሕገ ጠባይዓዊን (የተፈጥሮ ሕግን) ሳያፋልስ በማኅፀነ ድንግል ተቀረጸ (ተፀነሰ) ሲል ነው::[216]

ከላይ ከገለጥነው አማናዊ ትምህርት ውጭ ግን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአዳም መርገም (ጥንተ አብሶ) ነበረባት ማለት

[315] *ቅዱስ ያሬድ*፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 94፣ 379:

[216] *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 65::

ቃለ መጻሕፍትን ማስተሐቀርና ማሳበልም ነው:: ከዚህም ጋር ዳግማዊ አዳም የተባለ ክርስቶስን ያስገኘች ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ቀዳማዊ አዳም ከተገኘባት ከመጀመሪያይቱ ምድር ታንሳለች ማለትም ነው:: ይህ ከሆነ ደግሞ በምሥጢረ ድኅነት አስተምህሮ መሠረት ከምታንሰው ምድር (ከድንግል ማርያም) የተወለደው ሁለተኛው አዳም ክርስቶስ ከምትበልጠው ምድር (ከመጀመሪያይቱ ምድር) የተገኘውን ፊተኛው አዳምን እንደምን አድርጎ ማዳንና ማክበር ይቻለዋል? በዚያውስ ላይ መርገም ከወደቀባት ምድር (ከእመቤታችን) የተወለደው መድኅን ክርስቶስ እርግማን ካልወደቀባት ንጽሕት ምድር (የመጀመሪያዋ ኅትምት ምድር) የተገኘ አዳምን እንዴት አድርጎ ከእርግማን ሊዋጀውና ሊክሰውስ ይችላል?(217)

እኛስ በመልአኩ ብሥራት በቅዱስ ገብርኤል እንደበት "ዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል፤ ስለዚህ ደግሞ ካንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" (ሉቃ. 1÷35) ተብሎ የተሰበከልንን፤ እንዲሁም ደግሞ ከሣቴ ምሥጢር የሆነው ማኅየዊ መንፈስ ቅዱስ በቅድስት ኤልሳቤጥ አድሮ "ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ፤ አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ ማለትም መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ፤ በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን እያማለድሽ የምታሰጭ ነሽ:: ዳግመኛም ፍሬ ማኅፀንሽ የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መርገመ ሥጋን፣ መርገመ ነፍስን የሚያርቅ፤ በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን የሚያድል ቡሩክ አምላክ ነው (ሉቃ. 1÷42) በማለት የገለጠልንን አማናዊ ምሥጢር መሠረት፣ ምስክር አድርገን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ንጽሕት፣ ፍጽምት፣ ቅድስት፣ ኅትምት ምድር እንላታለን:: ዳግመኛም ከእርሷ ባሕርይ የተገኘውንና የተወለደውን መሲሕ ክርስቶስን ደግሞ ንጹሕ፣ ፍጹም፣ ቅዱስ፣ ክቡርና ኃያል ቡሩክ አምላክ ብለን እናምናለን፣ እናሳምናለንም::

(217) St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 24.



ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊም ስለ እመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና ባስተማረበት የነገረ ማርያም መድበሉ ሲናገር "የመጀመሪያይቱን ኅትምት ምድር ቀዳማዊ አዳምን ታስገኝ ዘንድ የቀረባትና የተገናኛት ማን ነው? ዳግመኛስ ዕፀ ሳቤቅን በይስሐቅ ፈንታ ቤዛ መሥዋዕት የሚሆነውን በግ ታስገኝ (ትውልድ) ዘንድ ማን አገዛት? በዚያውስ ላይ በአሽሞን በረሃ አንዳች ምክንያት ሳያስፈልግ ኅቱም ኰኵሕ (ዓለት) የውኃ ምንጭን እንደምን አድርጎ ሊያፈልቅና ሊያስገኝ ቻለ?"(218) ሲል የወላዲተ አምላክ ዘለዓለማዊ ድንግልና በዘመነ ብሉይ በተለያየ ኅብረ አምሳል የተገለጠ አማናዊ ምሥጢር መሆኑን መስክሮ አል:: ከዚህም ጋር ኅትምት ምድር፣ ዕፀ ሳቤቅ እንዲሁም ኅቱም ኰኵሕ (ዓለት) በዘመነ ሥጋዌ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም በኩል የሚፈጸመውን የድኅነተ ዓለም ምሥጢር አጉልተው የሚገልጹ በመሆናቸው የእመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና ምን ያህል ከነገረ ድኅነት ጋር የተያያዘ ጥልቅ ትሥሥርና ግንኙነት እንዳለው ይገነዘቧል::

## 4.1.2 በትረ አሮን (የአሮን በትር)

በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው የካህኑ የአሮን በትር የልዑል እግዚአብሔር ማደሪያና የክብሩም መገለጫ በሆነው በቤተ መቅደስ ውስጥ ሳለች ሳይተክሏትና ውኃ ሳያጠጧት እንደለመለመችና እንዳበበች፤ ፍሬም እንዳስገኘች እንመለከታለን:: (ዘኁ. 17÷8-9፤ ዕብ. 9÷4) ይህም ሊሆን የቻለው ከሃሌ ኩሉ (ሁሉን ቻይ) የሆነው አምላክ በትረ አሮንን ከሌሎቹ ነገደ እስራኤል በትሮች ሁሉ ይልቅ በማይመረመር አምላካዊ ጥበቡ ስለመረጣትና ስላከበራት ነው:: ከዚህም ድንቅ ምሥጢር ረቂቅና ጥልቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ጥበብ እንረዳለን፣ እንገነዘባለን:: ስለሆነም ይህ አማናዊ ምሳሌ በዘመነ ሐዲስ በድንግልናዊ ፅንጽና ልደት የሚገለጠውንና የሚፈጸመውን አምላካዊ የቸርነትና የማዳን ሥራ አጉልቶ የሚያሳይና የሚያስረዳ ወቋሔተ ምሥጢር ነው::

(218) Brock, *Bride of Light*, 150-151.

በዚህም መሠረት በትረ አሮን የወላዲተ አምላክ የድንግል ማርያም ምሳሌ ስትሆን፤ ፍሬው ደግሞ የፍሬ ሕይወት፣ ፍሬ መድኃኒት የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው::

ከላይ እንደገለጥነው በትረ አሮን ሳይተክሏትና ውኃ ሳያጠጧት በቤተ መቅደስ ውስጥ ሳለች ለምልማ፣ አብባና ፍሬ አፍርታ እንደተገኘ ች ሁሉ፤ አማናዊቷ በትረ አሮን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም በንጽሕና በቅድስና ሆና በቤተ መቅደስ ውስጥ ሳለች በማይ መረመር የመንፈስ ቅዱስ ግብር ያለ ዘር፣ ያለ ሩካቤ ፍሬ ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስን አስገኝታለች:: ይህንን ድንቅ ምሥጢራዊ ምሳሌ በመግለጥ "እግዚአብሔርም ሙሴን፦ የአሮንን በትር ወደ ምስክሩ ታቦት ፊት መልስ፤ ማጉረምረማቸው ከእኔ ዘንድ እንዲጠፋ እነርሱም እንዳይሞቱ ለሚያምኑብኝ ልጆች ምልክት ሆና ትጠበቅ አለው::" (ዘኁ. 17÷10) በማለት ሕገ ቤትስ የሆነችው ቅድስት ኦሪት ትመሰክራለች::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ማርያም አስተምህሮ ይህ አማናዊ ምሳሌ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ጥልቅ ምሥጢራዊ ግንኙ ነት ሲገልጥ የአሮን በትር በጥበበ እግዚአብሔር ማበቧ፣ መለምለማኗ ፍሬ በረከትን ማፍራቷ በእስራኤል ዘሥጋ ዘንድ ሰፍኖ የነበረውን ፍርሃትና ቀቢጸ ተስፋ ከእስራኤላውያን ልቡና አርቋል፣ አስወግዷል:: እንደዚሁም ሁሉ ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት በሰው ልጆች ላይ ሰልጥኖ የነበረው ኩነኔ ሞትና ፍርሃተ ሲኦል ከአማናዊቷ በትረ አሮን (የአሮን በትር) ከድንግል ማርያም በተገኘው (በተወለደው) ፍሬ ሕይወት፣ ፍሬ በረከት በሆነው በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተወግዶአል:: ከዚህም ጋር በትረ አሮን ያፈራችው የለውዝ ፍሬ ጥዑም እንደሆነ ሁሉ፤ በኃጢአትና በመርገም ምክንያት መራራ ሆኖ የነበረው የመላው ሰው ዘር ሕይወት ከአማናዊቷ በትረ አሮን ከወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በተገኘውና ፍሬ ጥዑም፣ ፍሬ ሕይወት፣ ፍሬ በረከት በሆነው አምላክ በመድኃኔዓለም ክርስቶስ ጣፍጧል::[219]

[219] ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 380:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ*



ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢረ ድኅነት አስመልክቶ በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ዘንድ ዘወትር የሚዘመረው የእመቤ ታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋና ሲገልጽ፦ "በትረ አሮን አንተ ሠ ረጸት ዘእንበለ ተክል ወኢሰቀይዋ ማየ:: ከማሁ አንቲኒ ኦ ወላዲተ ክርስቶስ አምላክነ ዘበአማን:: ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ ወለድኪዮ ለመድኅንነ፤ ሳይተክሏት የበቀለች፤ ውኃ ሳያጠጧት የለመለመች፣ ያበበችና ያፈራች የአሮን በትር ነበረች:: እውነተኛ አምላካችን ክርስቶስን የወለድሽልን ድንግል ማርያም ሆይ አንቺም እንደ እርሷ ነሽ:: ፍሬ ሕይወት የሆነው ጌታም ዘር ሩካቤ ምክንያት ሳይሆነው ካንቺ ሰው ሆኖ አዳነን::"[220] በማለት በአጽንኦት ይመሰክራል::

ሌላው ምሥጢር ደግሞ በትረ አሮን ሳይተክሏትና ውኃ ሳያጠጧት ለምልማና አብባ አሥራ ሁለት በኵረ ሎሚ አፍርታ እንደተገኘች፤ እንደዚሁም ሁሉ እመቤታችን ድንግል ማርያምም በቤተ መቅደስ አሥራ ሁለት ዓመት ኖራ ፍሬ ሕይወት ጌታን ያለ ዘር፣ ያለ ሩካቤ በኅቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ድንግልና ወልዳ አስገኝታለችና አማናዊት በትረ አሮን ትባላለች:: ከዚህም ጋር የአሮን ደቦስ (ደረቅ) በትሩ ከሌሎቹ ነገደ እስራኤል በትሮች ሁሉ ተለይታና ተመርጣ፣ በሐመልማል ተንቈጥቁጣ፣ በጽጌ አጊጣ እንደተገኘች ሁሉ፤ አማናዊት በትረ ቅዱሳን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምም ደብስተ እምኃጢአት (ከኃጢአት የራቀች) ሆና በድንግልና፣ በንጽሕናና በቅድስና አጊጣ፣ ከአንስተ ዓለም ሁሉ በልጣ ተገኝታለች::

ስለሆነም የአሮን በትር መለምለምና ማበብ ለእስራኤል ዘሥጋ የኃይልና የድል ምልክት እንደሆነ ሁሉ፤ እንዲሁም የእመቤታችን

*ሰዓታት*፣ ገጽ 295:: *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 202-204:: Brock, *Bride of Light*, 41-42, 101-102.

[220] *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 202-204፤ ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 386:: አባ ጽጌ ድንግል፣ "ማኅሌተ ጽጌ"፣ ገጽ 597:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 180:: ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፣ ገጽ 25:: Brock, *Bride of Light*, 101-102.

የቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና መፅነስና መውለድ ለእስራኤል ዘነፍስ ምእመናን የድኅነትና የሕይወት ምልክት ሆኗል:: ነቢየ እግዚአብሔር ልዑለ ቃል ኢሳይያስም በመንፈስ ትንቢት ተመርቶና ተቃኝቶ "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ÷ ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች÷ እግዚአብሔር ወልድንም ትወልዳለች÷ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች::" (ኢሳ. 7÷14) በማለት የተናገረው ትንቢታዊ ቃለ ተስፋ ይህንኑ ምሥጢር አጉልቶ ከማሳየቱና ከማስረዳቱም በላይ ወትረ ድንግል (ዘለዓለማዊት ድንግል) የሆነችው እመቤታችን በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ታላቅ ድርሻና መሠረታዊ ሚና በግልጥ ይመሰክራል::

ዳግመኛም ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ከላይ የጠቀስነውን የቅዱስ ኤፍሬምን ቃለ ውዳሴ መሠረት አድርጎ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት በአንቀጸ ብርሃን ድርሰቱ "በትረ አሮን አንተ ሠረፀት ዘእንበለ ተክል ወእንበለ ሠቀይዎ ማየ በቤተ መቅደስ:: ... ከማሁ አንቲኒ ነበርኪ ውስተ ቤተ መቅደስ በቅድስና ወበንጽሕ ... ወሠረፀ እምኔኪ ፍሬ ሕይወት ዘበልዐ ማእዝኑ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ:: ኦ ቅድስት ዘእንበለ ፈካቤ ዕክብኪ ወልደ፤ ሳይተክሏትና ውኃ ሳያጠጧት የለመለመችና ያበበች የአሮን በትር ነበረች:: አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ሆይ አንቺም እንደ እርሷ በንጽሕና በቅድስና ሆነሽ በቤተ መቅደስ ኖርሽ:: ... ከአንቺም እውነተኛ የሕይወት ፍሬ የሆነ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገኘ:: ቅድስት ድንግል ሆይ ዘር፣ ሩካቤ ምክንያት ሳይሆንሽ እግዚአብሔር ወልድን አስገኘሽ::"[221] በማለት ተናግሮላታል::

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የሚሳሉትና የብሥራተ መልአክን ምሥጢር የሚሰብኩት ኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳት ሥዕላት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ውስጥ ሳለች የመጋቤ ሐዲስ የቅዱስ ገብርኤልን ዜና ብሥራት እንደሰማችና መድኅን ክርስቶስን በኅቱም ድንግልና እንደፀነሰች ያስረዳሉ፣

[221] ቅዱስ ያሬድ፣ «አንቀጸ ብርሃን»፣ ገጽ 411::



ይመሰክራሉ:: ይኸውም ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትን ጠብቀው በሚሳሉት የብሥራተ መልአክ ሥዕላት ላይ ከእመቤታችን አጠገብ የሚታየው መንጦላዕተ ቤቱ መቅደስ (የቤተ መቅደስ መጋረጃ) እንዲሁም የቅዱሳት መጻሕፍት ማንበቢያ አትሮንስ የብሥራተ መልአክ ምሥጢር የተከናወነው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአሥራ ሁለት ዓመታት ያህል በንጽሕናና በቅድስና ጸንታ በኖረችበት ቤተ መቅደስ መሆኑን ያስረዳል::[222]

ከላይ እንደገለጥነው በትረ አሮን የምስክሩ ታቦት ባለበት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እንደተቀመጠችና በዚያም ሳለች ሳይተክሏትና ውኃ ሳያጠጧት አብባና ለምልማ ፍሬ በረከትን እንዳስገኘች ሁሉ (ዘኍ. 17÷1-11)፤ አማናዊቷ በትረ አሮን የሆነችው ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምም በንጽሕና፣ በቅድስና ጸንታ በቤተ መቅደስ ሳለች ያለ ዘርዐ ብእሲ ፍሬ ሕይወት የሚሆን ጌታን በማኅፀኗ አፍርታለች::[223]

ቅዱስ አባ ሕርያቆስም ይህንን ምሥጢር ሲያስረዳ፡- "ኦ ድንግል እኮ በተላህዮ ዘልሕቂ ከመ እዋልደ ዕብራውያን እለ ያገዝፉ ክሣዶን:: አላ በቅድስና ወበንጽሕ ውስተ ቤተ መቅደስ ነበርኪ፤ ድንግል ሆይ አንገታቸውን እንደሚያገዝፉ፤ አንድም ግዙፉን ልብ እንደሚሆኑ እንደ ዕብራውያን ሴቶች ልጆች በዋዛና በፈዛዛ፣ በቀልድና በጨዋታ ያደግሽ አይደለሽም:: ይልቁንም በቤተ መቅደስ በቅድስና በንጽሕና ኖርሽ እንጂ"[224] ሲል ተናግሮላታል::

[222] John Baggely, *Festival Icons for the Christian Year* (Crestwood New York: St. Vladimir's Seminary Press, 200), 16-20, 23-27. *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 125-126::*

[223] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት፣* ገጽ 148:: ቅዱስ ያሬድ፣ "አንቀጸ ብርሃን"፣ ገጽ 411:: Bauer, *The Essential Mary Handbook*, 38-39.

[224] *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 116-117::



**ሥዕል 8:- አማናዊት ቤተ መቅደስ ድንግል በቤተ መቅደስ**

"ኦ መቅደስ ዘኮነ ሰሲሁ እግዚአብሔር ሊቀ ካህናት፤ ማኅየዊ ጌታ በማኅፀን ያደረብሽ አማናዊት መቅደስ አንቺ ነሽ።"

(ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 195)

"ድንግል ሆይ ግዙፋን ልብ እንደሚሆኑ እንደ ዕብራውያን ሴቶች ልጆች በዋዛ፣ በፈዛዛ ያደግሽ አይደለሽም። በቅድስና፣ በንጽሕና በቤተ መቅደስ ኖርሽ እንጂ።"

(ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 116-117)



## 4.1.3 ፀምር ዘጌዴዎን (የጌዴዎን ፀምር)

በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው ከስምንቱ ብሔረ ኦሪት ማለትም (ከኦሪት ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኍልቍ፣ ዘዳግ ም፣ መጽሐፈ ኢያሱ፣ መጽሐፈ መሳፍንትና መጽሐፈ ሩት) መካከል አንዱ የሆነው መጽሐፈ መሳፍንት ሕዝበ እግዚአብሔር የሆኑት እስራኤላውያን በረድኤተ እግዚአብሔር አጋዥነት በጠላቶቻቸው በምድያማውያንና በአማሌቃውያን ላይ የተቀዳጁትን ድል ያወሳል። ከዚህም ጋር ለዚህ ሀብተ መዊዕና ኃይለ መዊዕ (የአሸናፊነት ኃይልና የድል አድራጊነት ሀብት) ዐቢይ ምልክትና ምክንያት የሆነችውን ፀምረ ጌዴ ዎንንም ይጠቅሳል። (መሳፍ. 6÷36-40) ይኸውም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ጌዴዎንን በመልአኩ አድሮ የእስራኤል ጠላቶች የሆኑትን አሕዛብን እንደሚያጠፋ በነገረው ጊዜ ጌዴዎን የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን በዘረጋት ፀምር (የተባዘተ የበግ ጠጉር) ላይ የድል ምልክት እንዲገልጥለትና እንዲያሳየው በትሕትና ሆኖ ጠይቋል። በዚህም መሠረት እግዚአብሔር አምላክ ጌዴዎን በፊቱ በዘረጋት ፀምር ላይ ብቻ ጠል አወረደ፤ ከፀምሩ ውጭ ባለው ምድር ላይ ግን ጠል አልወረደም። ዳግመኛም ጌዴዎን እግዚአብሔርን ጠል በዙሪያው ባለው በምድር ሁሉ ላይ እንዲወርድ፤ በፀምሩ ላይ ግን ፈጽሞ እንዳይወርድ ለመነ። ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔርም የጌዴዎንን ፈቃድ ፈቃዱ አድርጎ ፈጸመለት። በመጨሻም ጌዴዎን በፀምሯ ላይ የተገለጠውን አምላካዊ ትእምርተ መዊእ (የድል አድራጊነት ምልክት) ይዞ የሕዝበ እስራኤልን ጠላቶች ድል አድርጓል።

ብርሃነ ዓለም የተሰኘው ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ መፍቀሬ ሰብእ የሆነው እግዚአብሔር በዘመነ መሳፍንት ለጌዴዎን የገለጠው ይህ አማናዊ ምሳሌና ምልክት ኋላ በዘመነ ሐዲስ በምሥጢ ረ ሥጋዌ አማካይነት የሚፈጸመውን አምላካዊ የድኅነተ ዓለም ሥራ የሚያሳይና የሚያስረዳ መሆኑን አስገንዝቧል። ሐዋርያው ስለ አንቀጸ

ሃይማኖት ባስተማረበት ክታቡ (መልእክቱ) ሲናገር:- "እንግዲህ ምን እላለሁ? ስለ ጌዴዎንና ስለ ባርቅ ስለ ሶምሶንም ስለ ዮፍታሔም ስለ ዳዊትና ስለ ሳሙኤልም ስለ ነቢያትም እንዳልተርክ ጊዜ ያጥርብኛልና:: እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ÷ ጽድቅን አደረጉ÷ የተ ሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ ..." (ዕብ. 11÷32-33) በማለት መስክሮአል::

ከላይ በገለጥነው ኅብረ አምሳል መሠረት ፀምር የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስትሆን፤ ጠል ደግሞ ጠለ ሕይወት፣ ጠለ በረከት የተባለ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው:: ስለሆነም በመጀመሪያው ምልክት እንዳየነው ጠል ከሰማይ በፀምሯ ላይ ብቻ መወረዱ ጠለ ሕይወት የሆነው ሰማያዊው አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በእመቤታችን በድንግል ማርያም ማኅፀን ብቻ የማደሩና የመዋሐዱ ምሳሌ ነው:: በአንጻሩ ደግሞ ጠል በፀምሯ ዙሪያ ባለው ምድር ላይ አለመውረዱ ሰማያዊው ጠለ ሕይወት እግዚአብሔር ወልድ በሌሎች ሴቶች አለማደሩን ያስረዳል፣ ያመለክታል:: ይህ አማናዊ ምሳሌም ከፍጡራን ሁሉ መካከል ከወላዲተ አምላክ ከድንግል ማርያም በቀር ለመለኮት ማደሪያነት፣ ለአምላክ እናትነትና ለድኅነተ ዓለም መሣሪያነት በቅቶ የተገኘና የተመረጠ አንዳችም ፍጡር አለመኖሩን በግልጥ ያስገነዝባል፣ ያረጋግጣልም::(225)

ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ከላይ የገለጥነውን የፀምረ ጌዴዎንን ኅብረ አምሳል በተረጎመበት አንቀጽ:- "ርእየ ጠለ ኅበ ፀምር ባሕቲታ እንዘ የብስት ኵላ ምድር ይተረጎም በርእየ ጠለ መለኮት ውስተ ማኅፀነ ድንግል እንዘ ኵሎን አንስት ኢለከፋት እማንቱ በነጠብጣበ ኃይል ዘአርያም::»(226) ሲል በምሥጢር አራቆ ተርጉሞታል:: ከዚህም ጋር እመቤታችን ድንግል ማርያም "ስለ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ፤ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ሆይ ከአንተ ዘንድ የሚገኝ ጠለ ረድኤት

(225) ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 95-96:: ቅዱስ ያሬድ፣ መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ 93፣ 379-381:: አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ 612-613::
(226) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ "መጽሐፈ ምሥጢር" ["The Book of Mystery"]፣ ገጽ 93-94::



ሕይወታቸው ነውና:: አንድም ከአንተ የተገኘ ወልድ ሕይወታቸው ነውና::»(227) (ኢሳ. 26÷19) ሲል ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ እንደተናገረው፤ እንዲሁም ሊቀ ነቢያት ሙሴ "ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ፤ ወከመ ዝናም ውስተ ገዳም"፤ ቃሌ እንደ ክረምት ጠል ትወርድላችኋለች፤ አንድም መስክን እንደሚያጠጣና እንደሚያለመልም፣ አውሎ ነፋስና የመብረቅ ንውጽውጽታም እንዳልተቀላቀለበት የምሕረት ዝናብ ትምህርቴ ትፈሳለች (ዘዳ. 32÷2) ብሎ እንደመሰከረው፤ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በቅዱሳት መጻሕፍት ጠለ ሕይወት፣ ጠለ ምሕረት፣ ጠለ በረከት፣ ተብሎ የተነገረለትን አምላክ በኅቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ድንግልና መውለዷ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ከፍተኛ ድርሻ በሕጽንኦት ይመሰክራል::

ሌላው ደግሞ በሁለተኛው ምልክት እንዳየነው ፀምር የእመቤ ታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስትሆን ጠል ደግሞ የዘርዐ ብእሲ ምሳሌ ነው:: በመሆኑም ጠል ከፀምሯ ላይ አለመውረዱ ነገር ግን በዙሪያው ባለው ምድር ላይ ብቻ መውረዱ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ያለ ዘር፣ ያለ ሩካቤ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን በኅ ቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ደንግልና ለመውለዷ ምሳሌ ነው:: በአንጻሩ ደግሞ ጠል ከፀምሯ ውጭ ባለው ምድር ላይ መውረዱ ከእ መቤታችን ከድንግል ማርያም ውጭ ያሉ ሌሎች ሴቶች በተፈጥሮ ሕ ግና ሥርዓት መሠረት በዘር፣ በሩካቤ ለመውለዳቸው ምሳሌ ነው::(228) ዳግመኛም ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ይህንን ኃይለ ቃል በምሥጢር ሲያብራራ "ዝኒ ይተረጎም በነጠብጣበ ዘርዐ ሙላድ ዘልማድ ዘይከውን ውስተ ማኅፀኖን ለአንስተ ኵሉ ዓለም:: ወድንግልሰ ንጽሕት ሕርምት ይእቲ እምውእቱ ነጠብጣበ ዘርዕ ኢለከፋት ይእቲ እምግማኔ ወኢርስሐት ይእቲ በጥልቀተ ሥጋ»(229)

(227) ዕዝራ ሐዲስ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ትንቢተ ኢሳይያስ ንባቡና ትርጓሜው፣ (ጎንደር፤ ጎንደር ማተሚያ ድርጅት፣ 1996 ዓ.ም.)፣ ገጽ 181::
(228) ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 96-97:: አባ ጊዮርጊስ ሳግላዊ፣ [Abba Giyorgis Di Sagla]፣ መጽሐፈ ምሥጢር ["The Book of Mystery"] CSCO, 93-94.
(229) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ "መጽሐፈ ምሥጢር" ["The Book of Mystery"]፣ ገጽ 94::

በማለት ተናግሮአል:: ከላይ በገለጥነው ትርጓሜ ምሥጢር መሠረት ፀምረ ጌዴዎን ለእሥራኤል ዘሥጋ ትእምርተ መዊእ (የድል አድራጊነትና የአሸናፊነት ምልክት) እንደሆነች ሁሉ፤ አማናዊቷ ፀምር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም እሥራኤል ዘነፍስ ለተባሉ ምእመናነ ሐዲስ ለክርስቲያኖች ኃጢአትን፣ ሞትንና ጥንተ ጠላታቸው የሆነውን ዲያብሎስን ለማሸነፋቸውና ድል ለመንሣታቸው ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ በጸጋ የተሰጠች የሕይወትና የድኅነት ምልክት ናት::

ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት «ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር ወከመ ነጠብጣብ ዘያንጠበጥብ ዲበ ምድር ወይሠርፅ ጽድቅ በመዋዕሊሁ፤ ጠል ከሰማይ ወርዶ ከፀምር እንዲስማማ ማኅየዊ ጌታም በማኅፀነ ማርያም ያድራል:: ለስ ያለ ዝናብ ዘንቦ ከሰማይ ወርዶ ከምድር እንዲስማማ አንተ በአማን ንጹሕ ዝናም የሚባል ጌታ ምድር ጽምዕት ዘኢሳይያስ በምትባል በእመቤታችን ማኅፀን ያድራል:: ዳግመኛም በጌታ ዘመን የምሥራች ወንጌል ትነገራለች::»[230] (መዝ. 71÷6-7) በማለት ኃይለ ንባቡን በምሥጢር አስማምቶ ተርጉሞታል:: ይህም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ «ዝናም ንጹሕ ኀደረ ላዕሌሃ» ሲል ከዘመረው ቃለ ውዳሴ ጋር በምሥጢር የተስማማና የተገናዘበ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በፀምረ ጌዴዎን የተመሰለችበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ብእሴ እግዚአብሔር የሆነው ጌዴዎን ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ከእርሱና ከሕዝቡ ጋር በረድኤት አብሮ እንዳለና እንዳልተለያቸው በፀምሯ አማካይነት ተረድቶና አምኖ አረጋግጦአል:: በአንጻሩ ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለእስራኤል ዘነፍስ ምእመናን ትእምርተ ድኅነት (የድኅነት ምልክት) ሆና ከመሰጠቷም ሌላ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ባሕርይ በኩነት መዋሐዱን ያወቅንባትና የተረዳንባት ምክንያተ ድኅነት ወሕይወት ናት::

[230] መገ/ሙ·ረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 356-357::



ይህንን አስመልክቶ ከዐበይት ነቢያት መካከል አንዱ የሆነው ልዑለ ቃል ኢሳይያስ የቤተ ክርስቲያናችን መተርጉማን «ደረቅ ሐዲስ ኪዳን» ብለው በሚጠሩት ቃለ ትንቢቱ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ለተዋሕዶ መሠረት፣ ለድኅነተ ዓለም ምክንያት መሆኗን በመግለጥ «ስለዚህ ጌታ ራሱ ከሰማይ ምልክትን ይሰጣችኋል:: እነሆ ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች፤ በድንግልናም እግዚአብሔር ወልድን ትወልዳለች:: ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች::» (ኢሳ. 7÷14) ሲል በመንፈስ ትንቢት አሰምቶ ተናግሮአል:: ከዚህ መሲሐዊ ቃለ ትንቢትም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መድኅነ ዓለም፣ ቤዛ አዳም የሆነ ክርስቶስን እንበለ ዘርእ፣ እንበለ ሩካቤ በኅቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ድንግልና መውለዷ መፍቀሬ ሰብእ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው አምላካዊ የድኅነት ምልክት መሆኑን ይገነዘቧል::[231] ይህ አማናዊ ምሥጢረ ተዋሕዶም ድንግል ወእም (እናትም ድንግልም) ከሆነችው ወላዲተ አምላክ በሥጋ የተወለደው መድኃኒት ስሙ «አማኑኤል:- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለትም ከሥጋችን ሥጋን፣ ከነፍሳችን ነፍስን ነሥቶ ተዋሐደን» በሚለው የመጽሐፍ ትርጓሜ በመፈጸሙ፣ በመታተሙና በመደምደሙ ታውቋል::

መጻሕፍት አምላካውያት የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ማለትም አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን ሕገ እግዚአብሔርን ተላልፈውና ትእዛዘ እግዚአብሔርን አፍርሰው የሠሩት ኃጢአትና በደል ሞትን እንዳስከተለብን፤ ይኸውም ሞት የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር አንድነት መለየት መሆኑን በመተባበር ይመሰክራሉ:: ይሁን እንጂ በወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን (በምሥጢረ ሥጋዌ) በኩል የተደረገው አምላካዊ የድኅነት ጉዞ (ሐዲስ ተፈጥሮ) ዋነኛው ዓላማ አስከፊ የነበረውን ይህን የሰው ልጆችን የስሕተትና የድቀት ኑሮ ማደስ በመሆኑ የሰው ልጅ በድንግል ማርያም የድኅነት ምክንያትነት ወደ ቀደመ

[231] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 70:: አያሌው ታምሩ (ሊቀ ጠበብት)፣ ምልጃ፣ ዕርቅና ሰላም፣ ገጽ 59:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ መጽሐፈ ሰዓታት፣ ገጽ 180-181:: Bauer, *The Essential Mary Handbook*, 39.

ክብሩ፣ ወደ ጥንተ ርስቱ ተመልሶ ከፈጣሪው ጋር የነበረውን አንድነት አግኝቶአል:: በዚህም ምሥጢረ አድኅኖት መሠረት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ከፍተኛ አስተዋጽኦ መ ረዳትና መገንዘብ ይቻላል::

ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢረ ተዋሕዶ መልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ተልኮ በመጣ ጊዜ "ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ቡርክት አንቲ እምአንስት"፤ ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ክብር ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ፤ ልዑል እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው:: አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ ማለት መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ ነሽ፤ በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን እያማለድሽ የምታሰጪ ነሽ (ሉቃ. 1÷28) በማለት አብሥሯታል:: በዚህ ቃለ ውዳሴ ውስጥ "ጌታ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው" የሚለው ኃይለ ቃል ጥልቅ የሆነ የነገረ ድኅነት ትርጓሜ ምሥጢር አለው:: ይኸውም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በጥንተ ተፈጥሮ በአርአያውና በአምሳሉ አክብሮ የፈጠረውን የሰውን ልጅ በሐዲስ ተ ፈጥሮ አድሶና ቀድሶ ለማዳን ባደረገው የሥጋዌ ጉዞ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ሥጋንና ነፍስን በተዋሕዶ ነሥቶ ሰው በሆነ ጊዜ ፈጽሞ እንደተዋሐደን የሚያጠይቅ ዐቢይ ቃለ ብሥራት ነው::

ከዚህም ሌላ ፀምረ ጌዴዎን በሰማያዊው ጠል መመላቷ አማናዊቷ ፀምር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም በአምላካዊ ምልዓተ ጸጋና ክብር ፍጹም መመላቷንና መክበሯን ያስገነዝባል:: በአንጻሩ ደግሞ በፀምረ ጌዴዎን ዙሪያ ያለው ምድር ደረቅ መሆኑ ምልዓተ ጸጋና ምልዓተ ክብር አጥቶ፣ የእግዚአብሔር በረከት ጎድሎበት በኃጢአት ጉድጓድና በሞት አዘቅት ውስጥ በአስከፊና በአሰቃቂ ሁኔታ ይኖር የነበረውን የሰው ልጅ ሕይወት ያመለክታል::(232)

(232) *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 95-97::* Bauer, *The Essential Mary Handbook*, 39.



## 4.1.4 የተዘጋች የሕዝቅኤል ምሥራቃዊት ደጃፍ

ኦርቶዶክሳውያን የነገረ ማርያም ሊቃውንት ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና ባስተማሩበት የምሥጢር መድበላቸው ከዐበይት ነቢያት መካከል አንዱ የሆነው ነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል በአምሳለ ኆኅተ ምሥራቅ ኅትምት (በተዘጋች የምሥራቅ ደጃፍ ምሳሌ) ያየውን ይህን ድንቅ ራእይ ለድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና ሰጥተው በምሥጢር ተርጉመውታል:: የዚህ ራእይ ገጸ ንባብ እንዲህ ይላል:- "ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ፤ ተዘግቶም ነበር:: እግዚአብሔርም:- ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታ ልና ተዘግቶ ይኖራል::" (ሕዝ. 44÷1-2)

በዚህ ትንቢታዊ ራእይ ነቢዩ ሕዝቅኤል ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን በተዘጋ የምሥራቅ ደጃፍ መስሏታል:: የቤተ ክርስቲያናችን መተርጉማን እንደገለጹት ምሥራቅ የፀሐይ መውጫ፣ የብርሃን መገኛ እንደሆነ ሁሉ፤ አማናዊቷ ምሥራቅ እመቤታችንም የፀሐየ ጽድቅ የኢየሱስ ክርስቶስ መገኛ ናት::(233) ይህንን ምሥጢር አስመልክቶ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በነቢዩ በሚልክያስ አድሮ "ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች" (ሚል. 4÷2) ሲል ተናግሮአል:: ከዚህ ተስፋ ትንቢትም መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክር ስቶስ በኃጢአት ጨለማ ተውጠውና በሞት ጥላ ሥር ወድቀው ለሚኖሩ ሁሉ የሚያበራ እውነተኛ ፀሐይ፣ የጽድቅ ብርሃን መሆኑን ይገነዘቧል::

ዳግመኛም የዚህ ተስፋ ትንቢት ፍጻሜ በዘመነ ሐዲስ መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ለቅዱሳን ሐዋርያት ብርሃነ መለኮቱን በገለጠበትና

(233) ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ 92-93::* አያሌው ታምሩ (ሊቀ ጠበብት)፣ *ምልጃ፣ ዕርቅና ሰላም፣ ገጽ 59::*

ምሥጢረ መንግሥቱን ባሳየበት በታቦር ተራራ ተፈጽሟል:: ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ የዚህን አምላካዊ ተስፋ ትንቢት ፍጻሜ አስመልክቶ ሲናገር «በፊታቸውም ተለወጠ፣ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ::» (ማቴ. 17÷2) በማለት መስክሮአል:: ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ "ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ፤ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች::» (ራእ. 12÷1) ሲል በአጽንኦት ገልጾአል::

በእነዚህ ቃላተ መጻሕፍት መሠረት ለዘላለም የማይጠልቀ ውና በጨለማ ወድቆ ለነበረው ዓለም የሕይወት ብርሃንን ያበራው አማናዊው ፀሐየ ጽድቅ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአማናዊቷ ምሥራቅ ከድንግል ማርያም በመገኘቱ እመቤታችን ምሥራቅ ትባላለች፣ በምሥራቅ ትመሰላለች:: ዳግመኛም በጨለማ ተውጦ የነበረው ዓለም ማለትም በኃጢአት ወድቆ በፍዳና በመርገም ተይዞ የነበረው መላው የሰው ዘር በመሆኑ ምክንያት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ይህ አስከፊው የሰው ልጅ ታሪክ የተለወጠባት ምክንያተ ድኅነት፣ ምክንያተ ሕይወት ናት:: ከላይ በጠቀስነው የቅዱስ ዮሐንስ ራእይ ክፍለ ንባብ ውስጥ «... ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት::» (ራእይ 12÷14) የሚለው ኃይለ ቃል እመቤታችን ድንግል በክልኤ (በሁለት ወገን ማለትም በሥጋዋም በኅሊናዋም ድንግል) የመሆኗን ምሥጢር ይገልጻል::[234]

በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በስፋት የሚታወቀውና ዘወትር የሚዘመረው የእመቤታችን ምስጋና ይህንን ምሥጢር ሲገልጥ «... ኦ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ዘእንበለ ርኩስ:: ሠረቀ

(234) Brock, *Bride of Light,* 63, 101. St. Jacob of Serug, *On the Mother of God,* 45. Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia,* 70-73, 76-77, 81, 87-89. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God,* 49. አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፤ *ክብረ ድንግል*፣ (አዲስ አበባ፤ አፋ ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም.)፣ ገጽ 5::



ለነ እምኔኪ ፀሐየ ጽድቅ፤ ወአቅረበነ ታሕተ ክነፊሁ እስመ ውእቱ ፈጠረነ፤ አምላክን የወለድሽ ንጽሕት ድንግል ማርያም ሆይ ፀሐየ ጽድቅ ጌታ ካንቺ ተገኘ፣ ተወለደ:: በክንፈ ረድኤቱ፣ በክንፈ መስቀሉም አቀረበን፤ በጥንተ ተፈጥሮ፣ በሐዲስ ተፈጥሮ ፈጥሮናልና»[235] በማለት ይመሰክራል:: ይህ ቃለ ውዳሴ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የፀሐየ ጽድቅ የኢየሱስ ክርስቶስ መገኛ የሆነች አማናዊት ምሥራቅ መሆኗን ያስገነዝበናል:: ስለሆነም በዚህ አማናዊ ምሳሌ መሠረት ፀዳለ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ጠፈረ ሰማይ እንደማይሰነጠቅና አንዳችም ጉዳት እንደማይደርስበት፤ ይልቁንም ፀዳለ ብርሃኑ ለዓለም ሁሉ እንዲያበራ፤ እንደዚሁም ለሰው ልጆች ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ፀሐየ ጽድቅ የሆነ ጌታ ከአማናዊቷ ምሥራቅ ከእመቤታችን በተወለደ ጊዜ ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም፣ አልተሻረምም::

ከላይ እንደተመለከትነው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ከሥጋዌው አስቀድሞ ዓለምን በተስፋ ትንቢት በጐበኘ ጊዜ «... የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች፥ ፈውስም በክንፎችዋ ውስጥ ይሆናል» (ሚል. 4÷2) ሲል ተናግሮአል:: ይህንን ቃለ ትንቢት መሠረት በማድረግ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ሲመሰክር «ወአቅረበነ ታሕተ ክነፊሁ፤ በክንፈ ረድኤቱ፣ በክንፈ መስቀሉም አቀረበን» ብሏል:: መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በዕፀ መስቀል ላይ በሚፈጽመው አምላካዊ የቤዛነት ሥራ በጥንተ ተፈጥሮ በአርአያውና በአምሳሉ አክብሮ የፈጠረውን የሰውን ልጅ ዳግመኛ በሐዲስ ተፈጥሮ እንደሚፈጥረው ገልጾ ተናግሮአል:: በመሆኑም በዚህ የሐዲስ ተፈጥሮ ጸጋ ክብር ደቂቀ አዳምን በሙሉ በመስቀሉ ጥላ ሥር በሕይወትና በዕረፍት እንደሚሰበስብ ሲያስረዳ «እምከመ ተሰቀልኩ እምድር እስሕብ ኵሎ ኀቤየ፤ እኔም ከምድር ብቅ ከሰማይ ዝቅ ብዬ በመልዕልተ መስቀል በተሰቀልኩ ጊዜ ሁሉን በሀብተ መንፈስ ቅዱስ ወደ እኔ እስባለሁ፣ በረድኤት አቀርባለሁ» (ዮሐ. 12÷32) ብሎ በአጽንኦት ገልጾአል::

(235) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 148-149:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 378:: *መዝሙረ ድንግል*፣ ገጽ 49፣ 99:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 178::

ከዚህም ጋር በኅቱም ማኅፀን የተገኘው መድኅን ክርስቶስ የፈጸመውን ይህንን ምሥጢረ ድኅነት አስመልክቶ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሲያደንቅ «በከመ ኄሰነ እግዚአብሔር በበሊዓ ዕፀ ዕልወት ከማሁ ተሣሃለነ እግዚአብሔር በዕፀ መስቀል። በከመ ተከሥተ ዕርቃነ አዳም ማዕከለ ዕፀዊሃ ለገነት ከማሁ ተከሥተ ዕርቃነ ትስብእቱ ለመድኃኒነ ማዕከለ ጉባኤሆሙ ለማኅበረ እስራኤል»(236) ብሏል።

ዳግመኛም ነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል ባየው በዚህ ትንቢታዊ ራእዩ ማኅደረ መለኮት የሆነች እመቤታችን ድንግል ማርያምን ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በረድኤት በሚያድርበትና በሚገለጥበት ቤተ መቅደስ ይመስላታል። ምክንያቱም መቅደስ የልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ማደሪያ እንደሆነ ሁሉ አማናዊቷ ቤተ መቅደስ ድንግል ማርያምም እሳተ መለኮት የሆነውን ሰማያዊውን አምላክ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀኗ የተሸከመች አማናዊት ቤተ መቅደሱ ናትና። (ዘጸ. 25÷8፤ ዕን. 2÷20፤ መዝ. 45÷4፤ መዝ. 131÷13-14፤ ማቴ. 1÷18-23፤ ሉቃ. 1÷35)

ይህንን አስመልክቶ ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን ባመሰገነበት ውዳሴው «አንቲ ውእቱ ዘፃርኪ ዓምደ እሳት ዘርእዮ ሙሴ። ዘውእቱ ወልደ እግዚአብሔር መጽአ ወኃደረ ውስተ ከርሥኪ፤ ኮንኪ ታቦተ ለፈጣሬ ሰማያት ወምድር። ፃርኪዮ በከርሥኪ ተሰዓተ አውራኀ፤ አንቲ ማእምንት ለዘአያገምርዎ ሰማያት ወምድር፤ ሙሴ ያየውን የእሳት ዓምድ የተሸከምሽ አንቺ ነሽ፤ ይኸውም ሰው ሆኖ በማኅፀንሽ ያደረው አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ነው። ሰማይና ምድርን ለፈጠረ ለእርሱ ማደሪያ ሆንሽ። ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀንሽ ተሸከምሽው። ሰማይና ምድር የማይወስኑትን፣ ምሉዕና ስፉሕ የሆነውን ረቂቅ አምላክ ለመወሰን የታመንሽ አንቺ ብቻ ነሽ»(237) ብሎ የመሰከረላት ስለዚህ ነው።

(236) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *«መጽሐፈ ምሥጢር» ["The Book of Mystery"]*፣ ገጽ 97-98።

(237) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 164። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 278።



እስካሁን ድረስ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል ባየው ታላቅና ድንቅ ትንቢታዊ ራእይ መሠረት በምሥራቅ እንዲሁም በቤተ መቅደስ የተመሰለችበትን ምሥጢራዊ ምክንያት ተመልክተናል። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ ትንቢታዊ ራእይ ትርጓሜ መሠረት ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና የምታምነውንና የምታስተምረውን አማናዊ ምሥጢር እንመለከታለን።

ከላይ እንደገለጥነው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በነቢዩ አድሮ «ይህ በር ለዘላለም ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም» ሲል የተናገረው አምላካዊ ቃል እመቤታችን ድንግል ማርያም ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይፈታና ሳይለወጥ ለዘለዓለም በድንግልና ጸንታ የምትኖር ወትረ ድንግል ማርያም (ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም) መሆኗን ያስገነዝባል፣ ያረጋግጣልም። ይኸውም ቅድመ ፀኒስ (ከመፅነሷ በፊት)፣ ጊዜ ፀኒስ (በፀነሰች ጊዜ)፣ ድኅረ ፀኒስ (ከፀነሰችም በኋላ) ዘለዓለማዊት ድንግል ናት። ዳግመኛም ቅድመ ወሊድ (ከመውለዷ በፊት)፣ ጊዜ ወሊድ (በወለደች ጊዜ)፣ ድኅረ ወሊድ (ከወለደችም በኋላ) ወትረ ድንግል ማርያም (ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም) መሆኗን በግልጥ ይመሰክራል።

ከዚህም ጋር ራሱ ባለቤቱ «... ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል» በማለት ለአካላዊ ቃል መዝገብነት (ሰሌዳነት)፣ ለወልደ እግዚአብሔር ዙፋንነት የተመረጠው የእመቤታችን የድንግል ማርያም ማኅፀን ከፈጣሬ ፍጥረታት ከእግዚአብሔር በቀር ዕሩቅ ብእሲ ፈጽሞ የማያድርበት መቅደስ፣ ፍጡርም ደፍሮ የማይቀመጥበት የመለኮት ዙፋን መሆኑን አበክሮ አስረድቷል። ይኸውም አበው «በጳጳስ ወንበር ቄስ፤ በንጉሥ ወንበር ራስ አይቀመጥም» እንዲሉ፤ ድንግል ማርያም ከሴቶች ሁሉ መካከል ተለይታ የተመጠረችው እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ፣ ማኅደረ መለኮት፣ መዝገበ ቃል ለመሆን ብቻ እንጂ ወላዲተ ሰብእ ዕሩቅ ወይም እመ ዕሩቅ ብእሲ (የፍጡር እናት) እንድትሆን አይደለም።

በዚያውም ላይ ሊቁ "ኦ እንቀጸ መድኃኒት ዘኢይትረኃው ወናስግቲሃ በወሲደ አምላክ ሰባሴ ትስብእት»(238) እንዳለው ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር በተቀረጸበት ማኅፀን ዘርዐ ብእሲ አርፎበታል ማለት በራሱ ጸርፊት (ዘለፋ) ነው:: ምክንያቱም ፈጣሪ በነገሠበት ዙፋን ላይ ፍጡር ደፍሮ ሊቀመጥ ፈጽሞ አይችልምና ነው:: ስለዚህ በቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም አስተምህሮ መሠረት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ማኅተመ ድንግልና በሥልጣነ እግዚአብሔር የተዘጋ፣ በአምላካዊ ተአምር የተቆለፈና በመለኮታዊ ኃይል የታተመ መሆኑን ልብ ይሏል::

ከላይ በገለጥነው ትንቢታዊ ራእይ መሠረት ኃያሉ አምላክ በተዘጋው ምሥራቃዊ የቤተ መቅደስ በር መግባቱ የባሕርዩን ርቀት ያሳያል:: ይህ አምላካዊ ክሂሎትም ኋላ በዘመነ ሥጋዌ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ በሦስተኛው ቀን በኅቱም (በተዘጋ) መቃብር ከመነሣቱና ቅዱሳን ሐዋርያት ከትንሣኤው በኋላ በጽርሐ ጽዮን በዝግ ቤት ውስጥ ብቻቸውን ተሰብስበው ሳሉ በሩ እንደተዘጋ ገብቶ በመካከላቸው ከመገለጡ ምሥጢር ጋር ይገናዘባል::

ከዚህም ሌላ ጌታ እግዚአብሔር በተዘጋው የመቅደስ በር መግባቱ በኋለኛው ዘመን አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ እንበለ ዘርዐ፣ እንበለ ሩካቤ በኅቱም ማኅፀን ለማደሩ ምሳሌ ነው:: ዳግመኛም አምላከ እስራኤል የመቅደሱን በር ሳይከፍት መግባቱና መውጣቱ የእስራኤል ዘነፍስ (የምእመናነ ሐዲስ) ጌታ የሆነው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአማናዊቷ ቤተ መቅደስ ከድንግል ማርያም በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ፣ በኅቱም ድንግልና ለመወለዱ፤ እመቤታችንም በኅቱም ድንግልናዋ

(238) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *ኆኅተ ብርሃን ["The Portal of Light"]* ed. M. V. D. Oudenrijn *Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium*, vol. 208, *Scriptores Aethiopici*, t. 39-40 (text) (Louvain: Secretariat du CorpusSCO, 1960)፣ ገጽ 140:: *መጽሐፈ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው*፣ (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.)፣ ገጽ 447:: ቅዱስ ሳዊሮስ፣ "ስለ ኒቅያ ሃይማኖት"፣ *ሃይማኖተ አበው*፣ ገጽ 375:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 186:: አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ *ክብረ ድንግል*፣ ገጽ 5:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 171፣ 226::



ጽንታ ለመገኘቷ ምሳሌ ነው::(239)

ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም እናትነትን ስትታደል ድንግልናዋ ሳይሻር፣ ድንግልናን ስትታደል ደግሞ እናትነቷ ሳይቀር ነው:: በዚህም ታላቅና ልዩ አምላካዊ ጸጋ መሠረት እመቤታችን እናትነትን ከድንግልና፤ ድንግልናን ከእናትነት ጋር ደርባና አስተባብራ ይዛ በመገኘቷ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ "ድንግል ወእም፤ እናትም ድንግ ልም" ተብላ ትከበራለች፣ ትመሰገናለች:: ስለሆነም ይህ ታላቅና ልዩ ጸጋ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን በዚህ ዓለም ከነበሩ፣ አሁንም ካሉትና ወደፊትም እስከ ኅልቀተ ዓለም ድረስ ከሚኖሩ ሴቶች ሁሉ ልዩ ያደርጋታል:: ለዚህም ልዑለ ቃል ኢሳይያስ "እነሆ ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች፣ በድንግልናም እግዚአብሔር ወልድን ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" (ኢሳ. 7÷14) ሲል የአማኑኤል እናት እመቤታችን ድንግልናን ከእናትነት፣ እናትነትን ከድንግልና ጋራ አስተባብራና አንድ አድርጋ የያዘች መሆኗን የሰጠው አማናዊ ምስክርነት በቂ ማስረጃችን ነው::

ከላይ የተመለከትነው የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም አስተምህሮ ለምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት ምንጭና መሠረት በመሆኑ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ከመ ትኩኒ ወሬዛ ለሃይማኖት ዓባይ" በማለት በአጽንኦት መስክሮአል:: የዚህ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢርም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም "ድንግል ወእም፤ እናትም ድንግልም" መባሏ ልጇ ወዳጇ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "አምላክ ወሰብእ፤ አምላክም ሰውም" ለመባሉ መሠረት ነው:: ዳግመኛም ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወሰብእ ለመባሉ ወሰን፣ ድንበር፣ ፍጻሜ እንደሌለው ሁሉ፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ድንግል ወእም ለመባሏ ወሰን፣ ፍጻሜ የለውምና ሊቁ ወላዲተ አምላክን የታላቁ ሃይማኖተ ወንጌል መሪ፣ መቅድም፣ ምንጭ፣ መሠረት ብሏታል::

(239) *መጽሐፈ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 447-449:: *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 106::

በመሆኑም የእመቤታችን ማኅተመ ድንግልና በፀኒስና በወሊድ አለመለወጡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሷ ሰው በሆነ ጊዜ ባሕርየ መለኮቱ አለመለወጡን ያስረዳል:: ይህንን ዐቢይ እውነታ አስመልክቶ በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ዘንድ በስፋት የሚታወቀውና ዘወትር የሚዘመረው የእመቤታችን ምስጋና «የዚህ ዓለም ሴቶች በድንግልና ሳሉ ወተትን ማስገኘት አይቻላቸውም፣ አይሆንላቸውምም:: ምክንያቱም ወተት ባለበት ድንግልና ሲኖር ፈጽሞ አይችልምና ነው:: በእመቤታችን ዘንድ ግን ለሁሉ የሚያስደንቅ ዐቢይ ምሥጢር አለ:: ይኸውም በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ከመውለዷ ጋር የድንግልናዊ ወተትን ደርባ የማስገኘቷ ምሥጢር ነው»(240) በማለት ያደንቃል::

ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም በነቢዩ በሕዝቅኤል የተነገረውንና ስለ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና የሚመሰክረውን ትንቢታዊ ራእይ መሠረት በማድረግ በውዳሴ ማርያም ድርሰቱ እንዲህ ብሏል:- «ሕዝቅኤል ነቢይ ኮነ ስምዐ በእንቲአሃ፤ ወይቤ ርኢኩ ኆኅተ በምሥራቅ ኅቱም በዐቢይ መንክር ማኅተም:: አልቦ ዘቦአ ዘእንበለ እግዚአ ኃያላን:: ቦአ ውስቴታ ወወፅአ፤ ነቢዩ ሕዝቅኤል እመቤታችን ዘላለማዊት ድንግል የመሆኗን ነገር በድንቅ ቁልፍ የተቈለፈች ደጅ በምሥራቅ አየሁ ብሎ ተናገረ:: ወደ እርሷም ከኃያላን ጌታ በቀር ሳይከፍታት ገብቶ ሳይከፍታት የወጣ የለም:: ይልቁንም ልዑለ ባሕርይ የሚሆን እርሱ ብቻ ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት ወጣ እንጂ::»(241)

(240) Sergius Bulgakov, *The Orthodox Church* (Crestwood, New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1988), 17. Karl Rahner, *Mary Mother of the Lord: Theological Meditations* (Edinburgh: Herder, 1963), 12-15. Brock, *Bride of Light*, 35, 100. St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 20. ቅዱስ ቴዎዶጦስ ዘዕንቄራ፣ "ስለ ምሥጢረ ልደት"፣ *ሃይማኖተ አበው*፣ ገጽ 172:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 37:: *መጽሐፈ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 447-448:: አያሌው ታምሩ (ሊቀ ጠበብት)፣ *ምልጃ፣ ዕርቅና ሰላም*፣ ገጽ 59:: *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 68:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 226::

(241) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 113-114:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን*፣ ገጽ 257:: *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 106::



በዚህ ቃለ ውዳሴ መሠረት ቤት የእመቤታችን፣ መቈለፊያው የማኅተመ ድንግልናዋ፣ እግዚአ ኃያላን ደግሞ የጌታ ምሳሌ ነው:: ይህ ትንቢታዊ ራእይ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ጥልቅ ምሥጢር በመግለጥ የቤተ ክርስቲያናችን መተርጉማን ዛሬ እሥራኤል ዘነፍስ የተባሉ ምእመናነ ሐዲስ ወደ ቤተ ክርስቲያን በምዕራብ በኩል አድርገው ወደ ምሥራቅ መግባታቸው ርደተ ገሃነም እንደቀረላቸው ያጠይቃል ሲሉ በምሥጢር ተርጉመውታል::

## 4.1.5 ደብር ነዋኂት ዘዳንኤል (የዳንኤል ረጅም ተራራ)

ቀደም ብለን በክፍል 3.1.4 ላይ እንደተመለከትነው ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤል የሰው እጅ ሳይነካውና ሳይፈነቅለው ከረጅም ተራራ ላይ ስለወረደው ድንጋይ በተናገረበት ትንቢታዊ ራእይ ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነት መመስከሩን አውስተናል:: ነቢዩ ያየው ይህ ድንቅ ትንቢታዊ ራእይ ከነገረ ድኅነት ምሥጢር ጋር ያለውን መሠረታዊ ግንኙትና ትሥሥርም አይተናል:: አሁን ደግሞ ይኸው ታላቅ ነቢይ የተመለከተው ራእይ የወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና የሚመሰክርና ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ጥልቅ ምሥጢርም አያይዞ የሚያስረዳ መሆኑን እንመለከታለን:: (ዳን. 2÷31-35)

ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በኋለኛው ዘመን በእመቤታችን በኩል ይፈጽመው ዘንድ ያለውን አምላካዊ የቤዛነትና የቸርነት ሥራ በነቢዩ አድሮ ገልጾአል:: በዚህም መሠረት ረጅሙ ተራራ የድንግል ማርያም ምሳሌ ሲሆን፤ የተራራው ርዝመት ወይም ታላቅነት ደግሞ እመቤታችን እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ ለመሆን የበቃችበትንና የታደለችበትን ልዩ አምላካዊ ጸጋና ፍጹም ክብር እንዲሁም ልዕልናዋን ያጠይቃል:: ከዚህም ጋር የሰው እጅ ሳይነካውና ሳይፈነቅለው ከተራራው

የወረደው ድንጋይ ዕብነ ሕይወት፣ ዕብነ መድኃኒት የተባለ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ይህ ታላቅ ድንጋይ ከረጅሙ ተራራ ወደ መሬት መውረዱ ወልደ እግዚአብሔር ከልዕልና ወደ ትሕትና መውረዱን ማለት ልዑል ባሕርዩን ዝቅ አድርጎ ከባሕርይ አባቱ ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ በፍጹም ትሕትና ወደዚህ ዓለም መምጣቱን ያመለክታል። ድንጋዩ የሰው እጅ ሳይነካው ወርዶ ምስሉን እንዳደቀቀውና እንደፈጨው ሁሉ፤ የማዕዘን ራስ ድንጋይ የሆነው መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስም ልማደ አንስት ሳያገኛት፣ ዘር ሩካቤ ምክንያት ሳይሆናትና በእደ ብእሲ መዳሰስ ሳይኖርባት በንጽሕና በቅድስና ጸንታ ከምትኖር ከቅድስት ድንግል ማርያም በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ፣ በኅቱም ድንግልና ተወልዶ፣ የሰውን ልጅ ከኃጢአት ባርነት፣ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነጻ አድርጎ ዓለምን አድኖአል።(242)

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ይህንን ትንቢታዊ ራእይ ከዘመነ ሐዲስ የሥጋዌ ምሥጢር ጋር አይይዞ ሲናገር «ዘውእቱ ዕብን ዘርእዮ ዳንኤል ነቢይ ዘተበትከ እምደብር ነዋኅ ዘእንበለ እድ። ዘውእቱ ቃል ዘወፅአ እምኅበ አብ። ወፅአ ወተሰብአ እምድንግል ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ወአድኃነነ፤ ነቢዩ ዳንኤል ያየው፣ የሰው እጅ ሳይነካውና ሳይፈነቅለው ከረጅም ተራራ የወረደው ድንጋይ ከአብ ዘንድ ወደዚህ ዓለም የመጣውና ዘር፣ ሩካቤ ምክንያት ሳይሆነው ከድንግል ማርያም ተወልዶ ያዳነን ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ነው»(243) በማለት መስክሮአል። ይህ ቃለ ውዳሴ የነቢዩ ትንቢታዊ ራእይ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ጥልቅ ግንኙነት በመግለጥ በምሥጢር ሲተረጉም ከረጅም ተራራ የወረደው ድንጋይ ከመንበረ ጸባዖት ወደዚህ ዓለም በትሕትና የመጣው የአካላዊ ቃል የእግዚአብሔር ወልድ ምሳሌ ሲሆን፤ ድንጋዩ የሰው እጅ ሳያስፈልገውና ሳይፈነቅለው ከረጅሙ ተራራ መውረዱ ደግሞ ወልደ እግዚአብሔር ከአማናዊቷ ነዋኂት ደብር (ረጅም ተራራ) ከድንግል ማርያም እንበለ ዘርእ ብእሲ ተፀንሶ ለመወለዱ

(242) O' Carroll, *Theotokos: A Theological Encyclopedia of the Blessed Virgin Mary,* 190. *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 66-72።
(243) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 66-67፣ 72።



ምሳሌ መሆኑን ይገልጻል።

ዳግመኛም ይኸው ሊቅ «... ኦ ዝ መንክር ልደተ አምላክ እማርያም እምቅድስት ድንግል። አግመረቶ ለቃል። ሊቀደሞ ዘርዕ ለልደቱ ወሊአማስኖ በልደቱ ድንግልናሃ። እምኅበ አብ ወፅአ ቃል ዘእንበለ ድካም። ወእም ድንግል ተወልደ ዘእንበለ ሕማም፤ ንዕድ፣ ክብርት፣ ልዩ ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ይህ የአምላክ መወለድ ምን ይረቅ? ምንስ ይጠልቅ? አካላዊ ቃልን በማኅፀኗ ወሰነችው፣ ፀነሰችው። ከእርሷ ለተወለደውም ልደት ዘርዕ፣ ሩካቤ ምክንያት አልሆነውም፤ በመወለዱም ማኅተመ ድንግልናዋን አልለወጠውም። አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ዘእምአካሉ ባሕርይ ዘእምባሕርዩ ድካም ሳይሰማው ተወለደ። በኋለኛው ዘመን አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከድንግል ማርያም ሕማመ ወሊድ ሳይሰማት፤ እርሱንም ሕፃናትን የሚሰማ ሳይሰማው ተወለደ»(244) ሲል በአጽንኦት ቃል መስክሮአል።

ኦርቶዶክሳውያን የቅዱሳት ሥዕላት ሊቃውንት [Orthodox Iconographers] ይህንን ረቂቅና ድንቅ የሆነውን የነገረ ማርያም አስተምህሮ ምሥጢረ ልደትንና የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት በሚገልጡት ሥዕላት አማካይነት በሰፊው ያስተምራሉ። ይኸውም በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ትውፊት መሠረት የሚሳለው የልደት ሥዕል ሕፃኑ ክርስቶስ በቤተ ልሔም ግርግም በእንስሳት መካከል ተኝቶ፣ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ደግሞ በአጠገቡ ቆማ ወይም ደግሞ በክንዶቿ እንደታቀፈችው ተቀምጣ ያሳያል። ይህ ዓይነቱ ትውፊታዊና ኦርቶዶክሳዊ ሥዕል ምሥጢራዊ ትርጓሜው ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ እንበለ ፃዕር ወሕማም (ያለ ምጥና ያለ ጭንቀት) መውለዷን ያመለክታል።(245)

(244) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 128። ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣* ገጽ 382።
(245) Baggely, *Festival Icons for the Christian Year,* 39. Nouwen, ***Behold the Beauty of*** *the Lord: Praying with Icons,* 33.

እንደሚታወቀው በተፈጥሮ ሕግና ሥርዓት መሠረት ወሊድ ምጥና ሕመም ያለበት እጅግ ከባድና አድካሚ የሆነ አስጨናቂ ግብር ነው:: ይህም ሊሆን የቻለው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ከስሕተተ ኃጢአትና ከድቀተ ዓለም በኋላ ቀዳሚት ሔዋንን «በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ» (ዘፍ. 3÷16) ብሎ ስለፈረደባት ነው:: ይሁን እንጂ ይህ አምላካዊ ፍርድ የኃጢአት ፍሬ፣ የመርገም ውጤት ቢሆንም ቅሉ ዳግሚት ሔዋን ድንግል ማርያም በንጽሐ ሥጋ፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ልቡና ያጌጠችና የተሸለመች በመሆኗ ይህ ሁሉ አልደረሰባትም:: ስለሆነም ምሥጢረ ልደትን በሚገልጡት ኦርቶዶክሳውያን ሥዕላት እመቤታችን ድንግል ማርያም ቆማ ወይም ተቀምጣ መታየቷ ቅድመ ዓለም ከባሕርይ አባቱ ከአብ እንበለ ድካም የተወሰደውን አምላክ ድኅረ ዓለም እንበለ ጻዕር፣ እንበለ ሕማም እንደወለደችው ለማጠየቅ ነው::

ቀዳሚት ሔዋን ምክረ ከይሲን (የጠላት ዲያብሎስን ክፉ ምክር) ሰምታ ወንድሙ አቤልን በግፍ የገደለ ቃየንን በጭንቅ፣ በጻዕርና በሕማም ወለደች:: በአንጻሩ ደግሞ ዳግማዊት ሔዋን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ክቡርና ገናና የሆነውን የመልአክ ሰላም የቅዱስ ገብርኤልን ዜና ብሥራት ሰምታ «ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ» ብላ በመቀበሏ ስለወገኖቹ ተላልፎ የሞተውንና በሞቱ ሞትን ደምስሶ ሕይወትን የሚሰጠውን አምላክ ያለ ሕማምና ያለ ጭንቅ ወልዳለች::

ይህንን አንጻራዊ የነገረ ድኅነት ምሥጢር አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን ባመሰገነበት ውዳሴው ሲናገር «... ዘፈትሐ ላዕለ ሔዋን ትለድ በጻዕር ወሕማም:: እንቲአ ማርያም ሰማዕኪ ዘይብል ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ:: ወለድኪ ለነ ንጉሠ እግዚአ ኵሉ ፍጥረት መድኅነ ወአድኃነነ፤ ቀዳሚት ሔዋን በሕማም ለዲ (በጻር፣ በምጥ ውለጂ) የሚል የመርገም ድምፅ ሰምታ ምክንያተ ሞት ቃየልን ወለደች፣ አስገኘች:: ዳግሚት ሔዋን ድንግል ማርያም ሆይ አንቺ ግን ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ፤ ምልዕተ ክብር፣ ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ውዳሴ የሆንሽ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ የሚል



የበረከት ድምፅን ሰምተሽ ፍጥረታትን ሁሉ የሚገዛ ሰው ሆኖ ያዳነን ንጉሥ ክርስቶስን ወለድሽልን፣ አስገኘሽልን::» (246) በማለት ዳግሚት ሔዋን እመቤታችን ምክንያተ ሕይወት፣ ምክንያተ ድኅነት ወበረከት መሆኗን አስረግጦ መስክሮአል::

በቤተ ክርስቲያችን ዘወትር የሚዘመረው የእመቤታችን ምስጋና ወላዲተ አምላክ ምክንያተ ድኅነት መሆኗን በመግለጥ ሲያስመግናት:- «... ኦ ዕሙቅ ብዕለ ጥበቡ ለእግዚአብሔር:: ከርሥ ዘፈትሐ ላዕሌሃ ትለድ በጻዕር ወሕማም ወኃዘነ ልብ:: ወኮነት ፈልፈለ ሕይወት:: ወወለደት ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ዘይሥዕር መርገመ እምዘመድነ፤ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር የጥበቡ ምልዓትና ስፋት ምን ይረቅ? ምንስ ይጠልቅ? በጻር፣ በምጥ ትወልድ ዘንድ የፈረደባት ማኅፀን የሕይወትና የድኅነት መገኛ ሆነች:: ከባሕርያችን መርገመ ሥጋን፣ መርገመ ነፍስን የሚያጠፋልንን ጌታን ዘር ምክንያት ሳይሆናት ወለደች» ይላል:: ዳግመኛም ሊቁ ኤራቅሊስ «ወኀበ እርዊ ምድር ቈዓ ሕምዘ በሲሰሚዐ ህየ ቃል በዊእ በሰሚዐ አሕየወ፤ ዲያብሎስ በአካለ ከይሲ ተሰውሮ፣ በልሳነ ከይሲ ተናግሮ የመርዙን ፈሳሽነት በሔዋን ጆሮ እንዳፈሰሰ፤ እንዲሁም ዳግሚት ሔዋን የተባለችው እመቤታችን የመልአከ ብሥራቷን የቅዱስ ገብርኤልን ቃለ ብሥራት ሰምታ በመቀበሏ ምክንያት አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በማኅፀኗ አድሮ አዳነን»(247) እንዳለ:: በዚህም ቃለ ውዳሴ መሠረት ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ረቂቅ በሆነው አምላካዊ ጥበቡ በድንግል ማርያም በኩል ባደረገው የሥጋዌ ምሥጢር የጠላት ዲያብሎስ ምክሩን እንዳፈረሰበትና እንደሻረበት፣ ለሰው ልጆችም ድኅነትንና ሕይወትን እንደሰጠ ይገነዘቧል::

ከላይ እንዳየነው የነቢዩ እግዚአብሔር ዳንኤል ትንቢታዊ ራእይ ቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም በእደ ብእሲ ሳትዳሰስ ዕብነ ሕይወት

(246) ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 165-166::
(247) ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 123:: ኤራቅሊስ፣ «በእንተ ምሥጢረ ትሥጉት»፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 162::

ወዕብነ ወድኅኒት የተባለ ጌታን እንበለ ዘርዕ በኀቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኀቱም ድንግልና በመውለዷ ምክንያት ድንግል ወእም የመሆኗን ምሥጢር በግልጥ ያስረዳል:: በዚህም ወላዲተ አምላክ ማርያም ድንግል በክልኤ (ድንግል በኅሊናሃ ወድንግል በሥጋሃ) መሆኗን በግልጥ የሚመሰክረውን የቤተ ክርስቲያናችንን የነገረ ማርያም አስተምህሮ አማናዊነት ልብ ይሏል::

ከዚህም ጋር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እመቤታችን እንበለ ሕማም ወዳዕር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የመውለዷን ምሥጢር በምሳሌ ሲያስረዱ የፊት ወዝ ከግምባር ሲወጣ ሕመም እንደማይሰማና ይህም ሲሆን በግምባር ላይ አንዳችም ጉዳት እንዳይደርስበት፤ እንደዚሁም መዓዛ ቅዱሳን የሆነው ምዑዝ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም፤ እመቤታችንም አንዳች ሕማም አላገኛትም ሲሉ አስተምረዋል:: ዳግመኛም የቤተ ክርስቲያን መተርጉማን በምሳሌ እንደገለጹት አንድ ሰው በመስታወት ጠቅላላ ሰውነቱን መስታወቱ ሳይሰበር ያየዋል:: ሲሄድም መስታወቱ ተሰብሮ አይወጣም:: እንደዚሁም ሁሉ ኃያልና ረቂቅ የሆነ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስተ ቅዱሳን፣ ከንጽሕተ ንጹሐን ከድንግል ማርያም ሥጋን፣ ነፍስን፣ ደመ ነፍስን ሲዋሐድ ማኅተመ ድንግልናዋን አላዛባም:: ይልቁንም ረቂቅና ድንቅ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ ግብር በኀቱም ድንግልና ተፀንሶ በኀቱም ድንግልና ተወለደ እንጂ:: ከዚህም ጋር መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በኀቱም ማኅፀን መገኘቱ (መወለዱ) ኋላ በዕለተ ትንሣኤ በኀቱም መቃብር ከመነሣቱ ምሥጢር ጋር የተገናዘበና የተሰናሰለም ነው::[248]

የቤተ ክርስቲያን መተርጉማን የእናታችን የሔዋን ከኀቱም ገቦ አዳም (የአዳም ጐን) ያለ ሕመምና ያለ ሕጸጽ መገኘት ዳግማዊ አዳም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኀቱም ማኅፀነ ማርያም እንበለ ሕማም፣ እንበለ ሕጸጽ ለመወለዱ ምሳሌ መሆኑን አስረድተዋል:: ከዚህም ሌላ

[248] Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 64, 87, 134-136. Brock, *Bride of Light*, 57. *መጽሐፈ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 449:: አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ *ክብረ ድንግል፣* ገጽ 5::



አባታችን አዳም ሔዋንን "የሕያዋን ሁሉ እናት" ሲል መሰየሙ (ዘፍ. 3÷20) ዳግሚት ሔዋን እመቤታችን እመ ሕይወት፣ እመ ሕያዋን መሆኗን በምሥጢር የሚያሳይ ቃለ ትንቢት ነው::[249]

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ማርያም አስተምህሮ እመቤታችን ወትረ ድንግል ማርያም (ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም) መሆኗን በግልጥ ይመሰክራል:: ይህም ማለት ቅድመ ጸኒስ (ከመፅነሷ በፊት)፣ ጊዜ ጸኒስ (በፀነሰች ጊዜ)፣ ድኅረ ጸኒስ (ከፀነሰችም በኋላ) ዘለዓለማዊት ድንግል ናት:: ዳግመኛም ቅድመ ወሊድ (ከመውለዷ በፊት)፣ ጊዜ ወሊድ (በወለደችም ጊዜ)፣ ድኅረ ወሊድ (ከወለደችም በኋላ) ወትረ ድንግል ማርያም ትባላለች:: ይኸውም ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓትንና ትውፊትን ጠብቀው በሚሣሉ ቅዱሳት ሥዕላት ላይ እንደምንመለከተው በእመቤታችን በግራና በቀኝ ትከሻዋ እንዲሁም በግምባሯ ላይ ያሉት ሦስት ብሩሃን ከዋክብት ወይም ደግሞ ብሩሃን መስቀላት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በሦስት ወገን ድንግል መሆኗን ማለትም ቅድመ ጸኒስ፣ ጊዜ ጸኒስ፣ ድኅረ ጸኒስ፤ አንድም ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ ዘለዓለማዊት ድንግል መሆኗን የሚያስረዱና የሚያስገነዝቡ ናቸው::[250] (ሥዕል 13 ይመልከቱ)

ከዚህም ጋር ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በሦስት ወገን ንጽሕት መሆኗን (ንጽሐ ሥጋ፣ ንጽሐ ነፍስ፣ ንጽሐ ልቡናን) አስተባብራና አንድ አድርጋ መያዟን ያስገነዝባል:: ዳግመኛም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ማኅደረ ሥሉስ ቅዱስ ማለትም የአብ፣ የወልድ፣

[249] *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 68:: *ተአምረ ማርያም፣* ገጽ 3-7:: St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 36-37.

[250] Michael Quenot, *The Icon: Window on the Kingdom* (Crestwood, New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1991), 121. Nouwen, *Behold the Beauty of the Lord: Praying with Icons*, 33. Baggley, *Festival Icons for the Christian Year*, 37. Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia* , 11, 83. Juniper B. Carol, *Fundamentals of Mariology* (New York: Benziger Brothers, Inc., 1956), 142-143. ቅዱስ ሲኖዶስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት፣* ገጽ 49-50:: *መጽሐፈ ቅዳሴ፣* ገጽ 37:: አባ ጽጌ ድንግል፣ "ማኅሌተ ጽጌ"፣ ገጽ 303-304::



ሥዕል 9:- ወትረ ድንግል ማርያም (ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም)

"ኦ እንቀጸ መድኃኒት ዘኢይትረኃው ወናስግቲሃ በወሊደ አምላክ ሰባሴ ትስብእት"

(ኖኅተ ብርሃን፣ ገጽ 140)

"ዐቀበ ድንግልናሃ ለወላዲቱ ቅድስት። ዝንቱ ውእቱ መንክር ልደት ዘይደሉ ለእግዚአብሔር፤ የንጽሕት እናቱን ድንግልና አጸና። ለእግዚአብሔር የሚገባ ድንቅ ልደት ይህ ነው።"

(ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 424)



የመንፈስ ቅዱስ ማረፊያና ማደሪያ መሆኗን ያስረዳል። ሌላው ምሥጢር ደግሞ ሦስቱ ብሩሃን ከዋክብት ወይም መስቀላት በእመቤታችን ላይ መታየታቸው ድንግል ማርያም ዳግሚት ሰማይ መሆኗንም ያሳያል። ለዚህም ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም "ኪሱ ሠራዊተ ሰማያት ይብሉ ብፅዕት አንቲ። ሰማይ ዳግሚት ዲበ ምድር፤ በሦስቱ ሰማያት ያሉ ቅዱሳን መላእክት ንዕድ ነሽ፣ ክብርት ነሽ እያሉ ያመሰግናሉ። ከምድር በላይ ያለች ሁለተኛ ሰማይ አንቺ ነሽና።"(251)

እንዲሁም ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ "አንቲ ውእቱ ህየንተ አርያም ዘበሰማያት ዘኮንኪ አርያመ በዲበ ምድር፤ ድንግል ሆይ በላይ በሰማያት ስላለ አርያም ፋንታ በምድር ላይ ያለ አርያምን የሆንሽ አንቺ ነሽ"(252)፤ ዳግመኛም የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ "መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ፤ መስቀል በከዋክብት እያበራ ሰማያትን አስጌጠ"(253) ሲሉ በአንድነት የሰጡት ምስክርነት በቂ ማስረጃ ነው። ከዚህም አማናዊ ምሳሌ ሰማይ አንድ ፀሐይን ብቻ እንጂ ሌላ ፀሐይ እንዳላስገኘ ሁሉ፤ አማናዊት ዳግሚት ሰማይ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ከአንዱ ፀሐየ ጽድቅ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ማንንም አላስገኘችም።

## 4.1.6 ለሔልቪዲየሳዊ የክሕደት ትምህርት [Helvidian Heresy] የተሰጠ ኦርቶዶክሳዊ መልስ

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዲሁም በዜና አበው ክፍለ ትምህርት በስፋት እንደተገለጸው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣውና ሔልቪዲየስ [Helvidius] የተባለው መናፍቅ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና የሚያሳብል የክሕደት ትምህርት አስተምሮአል። ይህ ሔልቪዲየስ በአራተኛው መቶ ክፍለ

(251) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 83-84፣ 173።

(252) ቅዱስ ያሬድ፣ "አንቀጸ ብርሃን"፣ ገጽ 402።

(253) *መጽሐፈ ቅዳሴ*፣ ገጽ 37። አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 17-20።

ዘመን የነበረ የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊ ነው:: በዜና አበው ጥናት [Patristic Studies] እንደምንረዳው ይህ ሔልቪዲየስ በ380 ዓ.ም. የወላዲተ አምላክን ዘለዓለማዊ ድንግልና የሚቃረን ጽሑፍ አዘጋጅቶ ነበር:: የጽሑፉ ዋና መልእክት በአጭሩ ምስጋና ይግባትና እመቤታችን ድንግል ማርያም ከልጇ ከወዳጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ጠባቂዋና አገልጋይዋ ከሆነው ከአረጋዊው ጻድቅ ከቅዱስ ዮሴፍ ሌሎች ልጆችን ወልዳለች የሚል ነው:: ሔልቪዲየስ ለዚህ ትምህርቱ እንደ ማስረጃ አድርጎ ያቀረበውም ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት «የጌታ ወንድሞች» እያሉ የሚያወሱትን የተወሰኑ ገጸ ንባባት ነበር::(254)

በአንጻሩ ደግሞ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ጠብቃ ይዛ የቆየችውን አማናዊ ትምህርቷን በመግለጥ በዘመኑ የነበረው ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ጀሮም [Jerome] ከላይ የተመለከትነውን ሔ ልቪዲየሳዊ የክሕደት ትምህርት በመቃወም በ383 ዓ.ም. በትንቢተ ነቢያት፣ በስብከተ ሐዋርያትና እንዲሁም ከእርሱ በፊት የተነሡ ቅዱሳን አበው ባስተማሩት አማናዊ ትምህርት ላይ የተመሠረተ ሰፊና ጥልቅ የሆነ የነገረ ማርያም መድበል ጽፎአል:: ይህ አባት የምሥጢር መድበሉን በትሑት ልቡና፣ በቀና መንፈስ አእምሮ ሲጀምር:- ["I must call upon the Lord Jesus to guard the sacred lodging of the womb in which He abode for nine months from all suspicion of sexual intercourse."] ይህም ማለት «ከሁሉ አስቀድሜ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ያደረበትንና የነገሠበትን ቅዱስና ኅቱም ማኅፀን ዘርዐ ብእሲ አርፎበታል፣ ወድቆበታል ከሚል ማንኛውም ዓይነት ጥርጥርና ክሕደት እንዲጠብቅና እንዲከለክል የግድ እጠራዋለሁ፣ እለምነዋለሁም»(255) ማለት ነው::

(254) St. Jerome, "The Perpetual Virginity of Blessed Mary," *A Select Library of the Christian Church: Nicene and Post-Nicene Fathers* eds. Philip Schaff and Henry Wace, Series 2, v. 6 (Peabody, Massachusetts: Hendrickson Publishers Inc., 1995), 334-346..

(255) St. Jerome, "The Perpetual Virginity of Blessed Mary," 335. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin,* trans. Matthias F. Wahba (Fr.) (Virginia: St. Athanasius' Coptic



በዚህ ንዑስ ርእስ ሥር የምንመለከተውን መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳብ በቀላሉ ለመረዳትና ለመገንዘብ እንዲቻል የሔልቪዲየስን የስሕተት ትምህርት እንዲሁም በዘመኑ የነበረው፣ የቤተ ክርስቲያን አባት ጀሮም የሰጠውን መጠነ ሰፊ ምላሽ እንመለከታለን:: ሌላው ደግሞ አበው «ለምኝ ሰው ዋሻ አታሳዩት፤ ቤቴ ነው ብሎ ያድርበታልና» እንዲሉ በዘመናችን አንዳንዶች የቅዱሳት መጻሕፍትን አስተምህሮ በሚገባ ካለማወቅና ምሥጢሩንም ጠንቅቆ ካለመረዳት የተነሣ ዛሬም በሔልቪዲየሳዊ የክሕደት ጐዳና ተጨልጠው የሚሔዱ አሉ::(256) ስለ ሆነም የሔልቪዲየስን የስሕተት ትምህርት በቀላሉ ለማስረዳትና ለማስገንዘብ እንዲቻል መሠረታዊ የሆኑትን ነጥቦች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች መድበን እናያለን:: ከዚህም ጋር በማያያዝ ለሦስቱም ሔል ቪዲየሳዊ የኑፋቄ ትምህርቶች ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት የሰጡትን ምላሽ በዝርዝር እንመለከታለን::

### 4.1.6.1 እመቤታችን ለአረጋዊው ጻድቅ ለቅዱስ ዮሴፍ መታጨቷ

የመጀመሪያው የሔልቪዲየስ አመለካከት ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ስለ ጌታችንና አምላካችን ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምድራዊ ሀረገ ትውልድ በጻፈበት አንቀጽ የተናገረውን ገጸ ንባብ መሠረት ያደረገ ነው:: ኃይለ ቃሉም «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበር:: እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች» (ማቴ. 1÷18) የሚል ነው:: ሔልቪዲየስ ይህን በመጥቀስ እመቤታችን ድንግል ማርያም ለአረጋዊው ጻድቅ ለቅዱስ ዮሴፍ መታጨቷ ወደ ፊት ወደ ጋብቻ ሊደርስ የሚችል መሠረታዊ ግንኙነት አለው ይላል:: ከዚህም ጋር እንደ ሔልቪዲየስ አባባል

Publishing Center, 1989), 5.

(256) Pope Shenouda III, *The Perpetual Virginity of the Virgin St. Mary* (Los Angeles: San Antonia Graphics, N/D), 1. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin,* 8. Pope Shenouda III, *Comparative Theology,* vol. I, 171.

ወንጌላዊው "... ሳይገናኙ ..." ማለቱ ወደፊት እመቤታችንና ቅዱስ ዮሴፍ አብረው ሊኖሩና ሊገናኙ (ሊቀራረቡ) የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ያመለክታል(257) ብሏል::

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ለዚህ ሔልቪዲየሳዊ አስተሳሰብ ምላሽ በሰጡበት አንቀጽ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ "... እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች" ሲል እመቤታችን ድንግል ማርያም ከጠባቂዋ ከቅዱስ ዮሴፍ ጋር ሳይቀራረቡና ሳይተዋወቁ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድን በግብረ መንፈስ ቅዱስ መፅነሷን መግለጡ እንጂ ድንግል ማርያምና ቅዱስ ዮሴፍ ከክርስቶስ ልደት በኋላ የግድ አብረው ይኖራሉ የሚል ፍቺ ፈጽሞ የለውም ብለዋል:: ከዚህም ጋር ጀሮም ለሔልቪዲየስ እንደገለጸለት ወንጌላዊው "ሳይገናኙ፣ ከመገናኘታቸው በፊት" የሚለውን ድርጊታዊ ቅደም ተከተልን አመልካች ቃል መጠቀሙ የሐሳብንና የድርጊትን ቅደም ተከተል ለማሳየትና ለማስረዳት መሆኑን ገልጿል:: ዳግመኛም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም መድኀኒ ዓለም ክርስቶስን ዘርዐ ብእሲ፣ ሩካቤ ምክንያት ሳይሆናት በድንጋሌ ሥጋ፣ በድንጋሌ ነፍስ ጸንታ መፅነሷንና መውለዷን ለማረጋገጥ መሆኑንም አስገንዝቧል::

ዳግመኛም ጀሮም ይህንን ትርጓሜ በሌላ አገላለጽ ሲያስረዳ "ሔልቪዲየስ ሳይጸጸትና ንስሐ ሳይገባ (ከመግባቱ በፊት) በሞት ተገታ፣ ተቀጠፈ፣ ተወሰደ" የሚል አንጻራዊ ምሳሌ ሰጥቶታል:: በመቀጠልም ይኸው አባት ሲናገር በዚህ አባባል መሠረት ሔልቪዲየስ ከሞተ በኋላ ሊጸጸትና ንስሐ ሊገባ ይችላል ማለት ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ነው ብሏል:: ይልቁንም ይህ አነጋገር ሔልቪዲየስ ንስሐ ሊገባ የሚችልበት አጋጣሚና ዕድል በሞቱ ምክንያት እስከ መጨረሻው ድረስ እንደተገታና እንደተዘጋ ያስረዳል፣ ያስገነዝባል:: እንደዚሁም ሁሉ የእመቤታችን የድንግል ማርያም በድንግልና መፅነስ ወላዲተ አምላክ የመሆኗን ብቸኛ

(257) St. Jerome, "*The Perpetual Virginity of Blessed Mary,*" 335-337. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*, 5-7.



ና ልዩ ምሥጢር ከመግለጡም በላይ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን ሊሽርና ሊለውጥ የሚችል አንዳችም ሰብአዊ ክስተት አለመኖሩን በአጽንኦት ይመሰክራል::(258)

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለቅዱስ ዮሴፍ አረጋዊ የታጨችበትን ዘርፈ ብዙ ምክንያት በዝርዝር ገልጸው አስረድተዋል:: በዚህም መሠረት እመቤታችን ለዮሴፍ የታጨችበት የመጀመሪያው ምሥጢራዊ ምክንያት ክርስት ገብቶ እንዲቆጠርላት ነው:: ለዚህም ወንጌላውያን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምድራዊ ልደቱን ቆጥረውና ዘርዝረው ሲጽፉ የእመቤታችንን ሀገረ ትውልድ በእጮኛዋ በቅዱስ ዮሴፍ ሀገረ ትውልድ አንጻር መቁጠራቸው በቂ ምስክር ነው::

እንደሚታወቀው በአይሁድ ሥርዓትና ልማድ መሠረት ሴቶች በትውልድ ሀረግ ውስጥ ገብተው መቆጠር ስለማይችሉ እመቤታችን ከዳዊት ቤት ለሆነው ለቅዱስ ዮሴፍ መታጨቷ በጌታችን ሀገረ ትውልድ ውስጥ ገብታ በዮሴፍ አንጻር እንድትቆጠር አድርጓታል:: ይህንንም ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምድራዊ ልደት በጻፈበት አንቀጽ "... ያዕቆብም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን ወለደ" (ማቴ. 1÷16) ሲል ገልጾአል::

የቤተ ክርስቲያናችን መተርጉማን እንደገለጹት የዚህ ሀረገ ትውልድ መገናኛው ጉንድ አልዓዛር ነው:: ይኸውም አልዓዛር ማትያንና ቅስራን ይወልዳል:: ማትያን ያዕቆብን፣ ያዕቆብ ዮሴፍን ይወልዳል፤ በአንጻሩ ደግሞ ቅስራ ኢያቄምን፣ ኢያቄም እመቤታችን ድንግል ማርያምን ይወልዳል:: ስለሆነም በዕብራውያን ሥርዓት ልማድ

(258) Matero, *Refuting the Attack on Mary: A Defense of Marian Doctrines* (San Diego: Catholic Answers Inc., 1999), 7-14. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*, 6-7. St. Jerome, "The Perpetual Virginity of Blessed Mary," 337-339.

መሠረት ወንድና ሴት አቀላቅሎ መቁጠር የለምና እመቤታችንን በዮሴፍ አንጻር ቈጠረ::[259]

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለቅዱስ ዮሴፍ የታጨችበት ሌላው ሁለተኛው ምክንያት ከደቂቀ አዳም ወገን የሆነች ሰብአዊ ፍጡር መሆኗን ለመግለጥና ለማረጋገጥ ነው:: ይኸውም እመቤታችን ከደቂቀ አዳም ወሒዋ ወገን የሆነች ብእሲት (ሴት) ባትሆን ኖሮ ለብእሲ (ወንድ) ባልታጨችም ነበር:: ስለሆነም ወላዲተ አምላክ ከደቂቀ አዳም ወገን ለሆነው ለቅዱስ ዮሴፍ መታጨቷ ሰብአዊ ተፈጥሮዋን ከማሳየቱም ሌላ እመቤታችን ሰማያዊት ፍጡር ወይም ኃይል አርያማዊት አለመሆኗን በማስረዳት ከደቂቀ አዳም ወገን አይደለችም የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት ለማረቅም ነው::[260]

ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ለአረጋዊው ጻድቅ ለዮሴፍ የታጨችበት ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ ብቻዋን ሳለች በመልአከ ሰላም በቅዱስ ገብርኤል ዜና ብሥራት መሠረት ፀንሳ ብትገኝ አይሁድ በሕጋቸው እንደተጻፈው አመነዘረች፣ ሴሰነች ብለው በድንጋይ ወግ ረው፣ በእሳት አቃጥለው እንዳይገድሏት ቅዱስ ዮሴፍ ምክንያት ሆኖ ያድናት ዘንድ ሥላሴ ባወቁ ገንዘብ በጥበብ ጠባቂዋና አገልጋይዋ ይሆን ዘንድ አጭተውለታል:: እመቤታችን ድንግል ማርያም ለቅዱስ ዮሴፍ እንድትታጭ ያስፈለገበት ሌላው አራተኛው ምክንያት ደግሞ በሚያስፈልጋት ነገር ሁሉ እንዲረዳት፣ እንዲታዘዛትና እንዲያገለግላት ነው:: ይልቁንም ደግሞ በመከራዋና በችግሯ ጊዜ ሁሉ አብሮ እንዲከተ ላት፣ እንዲያጽናናትና እንዲያረጋጋት ነው::[261]

[259] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 65:: ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 111-116::

[260] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 65:: Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers*, 40-41. St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 63. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*, 8.

[261] ተሸመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ ሰአሊ ለነ ቅድስት፣ ገጽ 16-19:: ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 65-66:: John McHugh, *The Mother of Jesus in the New*



በመሠረቱ መታጨት ለጋብቻ ሳይሆን ሰው ለሹመትም፣ ምርጥ ዕቃ ለመጠበቅም ይታጫል:: ለምሳሌ ያህል ታላቁ ሐዋርያ ብር ሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "እስመ ፈኀርኩክሙ ለአሐዱ ምት ድንግለ ወንጹሐ ክርስቶስ ከመ አቅርብክሙ ኀቤሁ፤ ወደ እርሱ አቀርባችሁ ዘንድ ለአንዱ ንጹሕ ድንግል ሙሽራ ለኢየሱስ ክርስቶስ አጭቻችኋለሁና" (2ኛ ቆሮ. 11÷2፤ ማቴ. 25÷1-13፤ ዮሐ. 3÷29፤ ኤፌ. 5÷26-27፣ 32) ብሏል:: ይኸውም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር አሮንን ከወንድሞቹ መርጦ፣ በትረ ሌዊን በሐመልማል አንቈጥቁጦ፣ በጽጌ አስጊጦ የድንግል ማርያም ምሳሌ የሆነችውን ደብተራ ኦሪትን (ቤተ መቅደስን) እንዲጠ ብቅና እንዲያገለግል እንደመረጠው፤ እንዲሁም ሥላሴ የዮሴፍን ንጽሕናውንና ቅድስናውን፣ ደግነቱን ባወቁ ገንዘብ ዕድሜው ከኢዮቤልዩ (ከኀምሳ) የተረፈ፣ ከስልሳ ያለፈ ይህን አረጋዊ ጻድቅ አማናዊት ቤተ መቅደስ ድንግል ማርያምን እንዲጠብቅና እንዲያገለግል ተመ ርጧል:: ይህም ይታወቅ ዘንድ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትን ጠብቀው በሚሣሉት ቅዱሳት ሥዕላት ላይ ቅዱስ ዮሴፍ በአምሳለ አረጋዊ ይታያል:: /ሥዕል 2 እና ሥዕል 4 ላይ ይመልከቱ/

ስለሆነም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር እንዲህ ባለ ረቂቅና ድንቅ ጥበቡ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን ለአረጋዊው ጻድቅ ለቅዱስ ዮሴፍ በአደራ መስጠቱ (ማጨቱ) ከላይ በገለጥናቸው አራት መሠረታዊና ዋና ዋና ምክንያቶች ነው:: በአጭሩ የእመቤታችን ጣዕመ ፍቅሯና ጣዕመ ውዳሴዋ የበዛለት ሊቁ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው "ኦ ድንግል አኮ ለዮሴፍ ዘተፍኅርኪ ለተቃርቦ:: አላ ከመ ይዕቀብኪ ንጹሐ:: እስመ ከማሁ ኮነ፤ ድንግል ሆይ ሀብትሽ ሀብተ ንጽሕ ሆኗልና ለዮሴፍ የታጨሽው ለግቢ (ለጋብቻ) አይደለም፤ በንጽሕና ሆኖ ሊጠብቅሽ ነው እንጂ"[262] በማለት ዘግቶታል:: ዳግመኛም እመቤታችን በቤተ ዮሴፍ

*Testament* (London: The Chaucer Press, 1975), 157-158. St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 61. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*. 8. Gaventa, *Mary: Glimpses of the Mother of God*, 43.

[262] ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 123::